# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ፤በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት**

**በአየለች ጨቃላ**

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ፤በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


**በአየለች ጩቃሳ**

**የጥናቱ አማካሪ**

**ግርማ ገብሬ (ዶ/ር)**



**መስከረም 2016 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# የፈታኞች ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ይህ ጥናት “አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ (በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት” በሚል ርዕስ አማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በአየለች ጨቃላ የቀረበው ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጧል፡፡

## የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ______________________ ፊርማ ___________________ ቀን____________

የውጭ ፈታኝ __________________ ፊርማ_________________ ቀን______________

የውስጥ ፈታኝ __________________ ፊርማ_________________ ቀን _____________

# ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይገባዋል፡፡

በመቀጠል ይህ ጥናት በመልካም ሁኔታ እንዲሳካና እንዲጠናቀቅ ሰፊ ጊዜቸውን በመስጠት አቅጣጫ በማስያዝና ማስተካከያ እየሰጡኝ እንዲሁም እያስተካከሉ ለረዱኝ አማካሪዬ ግርማ ገብሬ (ዶ.ር) ክብር ይስጥልኝ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ለጥናቱ ስኬት ውድ ጊዜያቸዉን በመስጠት መረጃ፣ አስተያየት፣ ሃሳብና እዉቀታቸውን በመስጠት ለተባበሩኝ የአርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የአሰተዳደር ሠራተኞችን በጣም አመሰግናለሁ፡፡

በሌላ በኩል የዚህ ጥናት ስኬት በስተጀርባ የአጥኚዋ ጥረት ብቻ ሳይሆን የቤተሰብና ሌሎች በቀናነት ይህ ጥናት እንዲጠናቀቅ ባደረጋችሁልኝ የተለያዩ ድጋፍና ትብብር ጥናቱ ይኸዉ ከግብ ደርሷል፡፡ ዉድ የሥራ ባልደረቦቼ መ/ርት ስንታየሁ ገብሩ፣ መ/ር ወንዱ ዘነበ፣ መ/ር አክሊሉ ኒኣ፣ መ/ር ሁሴን አህመድ እና ወጣት ወጋየሁ አንዱዓለም ላደረጋችሁልኝ ትብብር እጅግ በጣም አመሰግናችኋለሁኝ፡፡ በመጨረሻም ትምህርቴን ጀምሬ እስክጨርስ ድረስ በጉልበት፣ በሃሳብ፣ በገንዘብና በቁሳቁስ ድጋፍህ ሳይለየኝ እንዲሁም ቤተሰብን በመንከባከብ ከፈጣሪ ጋር አስጀምረህ ላስጨረስከኝ ባለቤቴ መ/ር ሚሊዮን ገ/ኪዳን እንዲሁም የእናትነትን ሚና በመቀበል ትልቅ ድርሻ የተወጣሽዉ ልጄ ተማሪ ሊዲያ ሚሊዮን የዘለዓለም ክብር ይገባችኋል እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ........................................ i

ማውጫ ........................................ ii

ሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ iv

አጠቃሎ ........................................ v

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

1.መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2

1.3 የጥናቱ አላማ ........................................ 4

1.3.1 የጥናቱ ዐቢይ አላማ ........................................ 4

1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች፡- ........................................ 4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 5

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 6

2. ክለሳ ድርሳናት ........................................ 6

2.1 የማዳመጥ ክሂል ምንነት ........................................ 6

2.2 የማዳመጥ ትምህርት ምንድን ነው? ........................................ 8

2.3 የማዳመጥ ክሂል የማስተማሪያ ዘመናዊ ዘዴዎች እና መመሪያዎች ........................................ 9

2.3.1 መመሪያ አንድ፡- በቅድመ- ማዳመጥ ጊዜ ........................................ 10

2.3.2 መመሪያ ሁለት፡- በማዳመጥ ጊዜ ........................................ 10

2.3.3 መመሪያ ሦስት፡ - (በድኅረ ማዳመጥ ጊዜ) ከማዳመጥ በኋላ ........................................ 11

2.4 ማዳመጥን የማስተማር አዳዲስ መንገዶች ........ 11

2.5 አዳምጦ የመረዳት ትምህርት ክንውን ደረጃዎች ........ 13

2.5.1. ቅድመ-ማዳመጥ ........ 13

2.5.2 የማዳመጥ ጊዜ ........ 15

2.5.3. በድህረ-ማዳመጥ ጊዜ ........ 17

2.6 የማዳመጥ ትምህርት አላማ ........ 19

2.7 የማዳመጥ ይዘት ምርጫ ........ 19

2.8. የማዳመጥ ይዘት ቅንብር ........ 23

2.9 የማዳመጥ ክሂል ማስተማርያ መሳሪያዎች ........ 24

2.9.1 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለጻዎች ........ 25

2.9.2 በመቅረጸ ድምጽ የተዘጋጁ ........ 25

2.9.3 በስእል፤ ካርታ ፤ሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁ ........ 26

2.9.4 ሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎች ........ 26

2.10 የማዳመጥ ንዑሳን ክህሎት ........ 27

2.10.1 ፍሬ ሀሳብ (ጭምቅ ሀሳብን) ማውጣት ........ 28

2.10.2 አውዱን መለየት ........ 28

2.10.3 ተዛማጅ ሀሳቦችን በየፈረጃቸው ማደራጀት ........ 28

2.10.4. መረጃ ለመፈለግ (ለማግኘት) ........ 28

2.10.5 ዝርዝር መረጃን መረዳት ........ 29

2.10.6 አጠቃላይ መረጃ (ግንዛቤ) ለማግኘት ........ 29

2.10.7 መገመት መቻል ........ 29

2.10.8 የሀሳብ አደረጃጀትን መረዳት ........ 30

2.11 ጥሩና ተደጋጋሚ ማዳመጥ በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ........ 30

2.12 የማዳመጥ ችሎታን የመገምገም ሂደት ........ 31

2.13 የማዳመጥ ግምገማ ዓይነቶች ........ 32

2.14 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 33

ምዕራፍ ሦስት ........ 35

3.የጥናቱ ዘዴ ........ 35

3.1 የጥናቱ ዐይነት ........ 35

3.2 የናሙና አመራረጥ ........ 35

3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 35

3.2.2 የመምህራን አመራረጥ ........ 35

3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 36

3.3 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 36

3.3.1 ምልከታ ........ 36

3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ ........ 37

3.3.3 ቃለ መጠይቅ ........ 37

3.3.4 የሰነድ ፍተሻ ........ 37

3.3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 38

3.4. የመረጃ አተናተን ........ 38

ምዕራፍ አራት ........ 39

4. የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 39

4.1 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 39

4.2 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ........ 41

4.3 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት የድህረ ማዳመጥ አተገባበር ........ 46

4.4. የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ የክፍል ዉስጥ አተገባባር ........ 50

ምዕራፍ አምስት ..... 54

5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 54

5.1.ማጠቃለያ ..... 54

5.2 የመፍትሔ ሐሳብ ..... 56

ዋቢ ጽሁፎች ..... 57

አባሪዎች ..... 59

# ሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሰንጠረዥ 4.1፡ የተጠኚ መምህራንና የትምህርት ቤት አደረጃጀት መግለጫን የሚያሳይ........39

ሰንጠረዥ4.2፡- የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ (ሁኔታ) ን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ፡-.......................40

ሰንጠረዥ 4.3፡ የክፍለ ጊዜዉ የቅድመ ማዳመጥ ክህሎት ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ምልከታ የተገኘ ምላሽ.....................................................................................42

ሰንጠረዥ 4.4፡ የክፍለ ጊዜዉ የቅድመ ማዳመጥ አተገባበር ከመምህራን የቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ.................................................................................................44

ሰንጠረዥ 4.5፡ የክፍለ ጊዜዉ የማዳመጥ ጊዜ ክሂል አተገባበር ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተደረገዉ ምልከታ የተገኘ ምላሽ..........................................................................47

ሰንጠረዥ 4.6፡ የክፍለ ጊዜዉ የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና .......................................................................................48

ሰንጠረዥ 4.7፡የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ ክህሎት ትምህርት አተገባበር ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተደረገዉ ምልከታ የተገኘ ምላሽ ...............................................51

ሰንጠረዥ 4.8፡ የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ ጊዜ አተገባበር በመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና። .....................................................................52

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በዋናነት አላማ ያደረገዉ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግምግማ ላይ ሲሆን ተጠኚዎቹ በአመችነት የናሙና አመራረጥ የተመረጡና ገላጭ የትንተና ዘዴን የተከተለ ጥናት ነዉ። ጥናቱም የተከናወነው በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፈት የሆኑ 75 በተመረጡ ተጠኚ ተማሪዎች ላይ ነዉ። አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃል መጠይቅና የክፍል ዉስጥ ምልከታ በማድረግ ሰብስባለች። በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ እንዲሁም በምልከታ በተገኘዉ ምላሽ በቅድመ ማዳመጥ ፣በማዳመጥ ጊዜ እና በድህረ ማዳመጥ ጊዜ ክፍል ዉስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል የመጠይቆቹን ጥያቄዎች በሰንጠረዥ ዉስጥ በቁጥርና በመቶኛ እንዲሁም በገለጻ ተተንትኗል። በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት በተገኙ የመረጃዎች ትንተና ዉጤት መሰረት ተጠኚ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ዉስጥ ሲተገበር የተገኘው ምላሽ እንደማይተገበርና ቢተገበርም አተገባበሩም ደካማ መሆኑ ከጥናቱ የተገኘዉ ዉጤት ያሳያል። ከተጠኚ መምህራን የተገኘ ምላሽም የማዳመጥ ክሂል ይዘቶችን በክፍል ዉስጥ የሚተገብሩት አልፎ አልፎ እንደሆነ በጥናቱ ዉጤት ታዉቋል። ሌላዉ መምህራን ከተማሪዎቹ ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ይዘቶችን በማዘጋጀት እንደማያቀርቡ በጥናቱ ዉጤት ዉስጥ ለማወቅ ተችሏል። እንዲሁም ተጠኚዎቹ ክሂሉን ለማዳበር ይችሉ ዘንድመምህራን ክሂሉን ሲተገብሩ የተለያዩ ስልቶችን ለምሳሌ የተቀረጹ ድምጾችን፣ አጫጭር ታሪኮችንና ሥነጽሁፋዊ ስራዎችን ወደ ክፍል ዉስጥ በማምጣት እንደማያስደምጧቸዉና በዚህም ምክንያት ዉጤታማነቱ ዝቅተኛ መሆኑን አጥኚዋ ተገንዝባለች። ከዚም በተጨማሪ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ትልቅ ተግዳሮት የሆነና ተጠኚ መምህራንም የገለጹት ጉዳይ፡- ተጠኚዎቹም ሆኑ ተማሪዎች ቋንቋዉን የሚማሩት እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ስለሆነ ተጠኚዎቹ ከወዲሁ የቋንቋዉ ትምህርት ይከብዳል፣ አይገባኝም በማለት እና ለቋንቋዉ ትምህርት ያላቸዉ ፍላጎት አናሳበመሆኑ ከየት መጣ የክሂሉን እዉቀት በታሰበዉ ልክ መተግበር አለመቻላቸዉን በጥናቱ ዉስጥ ተጠቅሷል። ሌላዉ ጉዳይ ለቋንቋዉ መምህራን ለክሂሉ መዳበርም ሆነ ለቋንቋዉ ትምህርት ዉጤታማነት አጫጭር ስልጠናና ዎርክ ሾፖች ስለማይሰጣቸዉ በክሂሉ አተገባባር ላይ ተጽእኖ እነዳሳደረባቸዉ በጥናቱ ዉስጥ ተረጋግጧ

# ምዕራፍ አንድ

# 1.መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ከአራቱ ቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ ማዳመጥ ነው፡፡ የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን Rixon (1986:3) "ማዳመጥ ማለት ለሚሰማው ጉዳይ ትኩረት በመስጠት የጉዳዩን ፍሬ ነገር ለመረዳት የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ በተለያዩ አላማዎች ላይ በመመስረት የሰዎችን ንግግር መርጦ በመስማት መልዕክቱን የመረዳት ሂደት ነው" በማለት ገልፀዋል፡፡

አራቱ የቋንቋ ክሂሎች መረጃ በመቀበልና መረጃ በማስተላለፍ በሁለት ይከፈላሉ፡፡ መረጃ መቀበያ ክሂሎች ማዳመጥና ማንበብ (receptive skills) ሲባሉ መናገርና መጻፍ ደግሞ መረጃ ማስተላለፍፊያ (productive skills) ይባላሉ፡፡ በሌላ በኩል ማዳመጥና መናገር በቋንቋ ውስጥ ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኙ ሲሆን ማንበብና መጻፍ ደግሞ በመደበኛ ትምህርት ሊገኙ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ማዳመጥና መናገር ትኩረት ሊሰጣቻዉ ይገባል (ማረዉ 1998፤206)፡፡

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ማዳመጥ አትኩሮትን የሚፈልግ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ ማረው (1998፣ 171-172) ማዳመጥ ከጠዋት እስከ ማታ ፣ ከዓመት እስከ ዓመት እድሜ ልኩን የሰው ልጅ የሚተገብረው ተግባር ነው፡፡ ማዳመጥ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ከማንኛውም የቋንቋ ክህሎት ይበልጡን በስፋት ያገለግላል፡፡ ይኸውም በአማካኝ ከምንናገረው ሁለት እጥፉን ከምናነበዉ አራት እጥፉን እንዲሁም ከምንፅፈው፣ ስምንት እጥፉን የበለጠ እንደ ምናዳምጥ በመግለፅ ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ የምንረዳው ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ ማዳመጥ የላቀ ድርሻ እንዳለው ያሳያል፡፡ በድሉ (1996፣ 45) የማዳመጥን ምንነት ሲገልፁ "ማዳመጥ በአእምሮአችን ውስጥ ንግግር ትርጉም የሚያስገኝበት ውስብሰብ ሂደት ነው፡፡ ጥሩ አድማጭ ከሚያዳምጠው አዲስ ሀሳብ ስለሚፈልግ አእምሮው ዘወትር ክፍት ነው፡፡… ጥሩ አድማጭ ለመሆን ደግሞ የማዳመጥ መንገድ ፣ በትምህርት መታገዝ አለበት" ይላሉ፡፡

እንደ Rixon (1986)፣ Underwood (1989) እና Richards (1983) አመለካከትም ጥሩ አድማጭ ለመሆን እንደማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ቋንቋን በዘልማድ ከአካባቢው ኅብረተሰብ ከመልመድ ያለፈ ትምህርት መቅሰም ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት ግን መደበኛ ትምህርት ያልተማሩ ወይም ለመማር እድል ያላገኙ ሰዎች ሁሉ ጥሩ አድማጭ አይደሉም ማለት እንዳልሆነ ሊስተዋል ይገባል፡፡ በተፈጥሯቸው ንቁ የሆኑ ጥሩ አድማጭ ሊሆኑ እንደ ማይችሉ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ቢሆንም ጥሩ አድማጭ ለመሆን ግን የማዳመጥ ክህሎት በትምህርት ቢዳበሩ የበለጠ ጠቀሜታ አለው፡፡ በ Underwood (1994:7) አገላለፅ "የማዳመጥ ትምህርት ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን፣ ራስን ለማስተዋወቅ፣ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ሰሜትን ለመጋራትና ራስን ለማዝናናት ጠቀሜታ ስላለው መዳበር አለበት፡፡

ይሁን እንጂ እንደ በርካታ የዘርፉ ምሁራን እምነት የዚህ ክህሎት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የተሰጠው አይደለም፡፡ ለአብነት ብንጠቅስ Kral (1996: 32) "በበርካታ አገሮች አዳምጦ መረዳት የተማሪዎች ችግር ነው" ይላሉ፡፡ በተጨማሪም ፍቅሩ (2002) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን የማስተማር ስነ ዘዴ (ቲም) ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ባዘጋጁት ጥናታዊ ጽሑፍ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ማዳመጥን በተግባር በመለማመድ የሚማሩበት ሁኔታ በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤቶች አነስተኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከተጠቀሱት ጥናቶች ለመመልከት እንደተቻለው የማዳመጥ ክህሎ ትምህርት ተገቢ ትኩረት የልተሰጠው መሆኑን ያመለከታል፡፡ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑትም እነዚህ ከተለያዩ አቅጣጫ ስለማዳመጥ ክህሎት ትምህርት አተገባበር ድክመት የተሰነዘሩ አስተያየቶች ሲሆኑ ይህ ጥናትም በጥናቶቹ ላይ እንደታየው ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የትኩረት ማነስ እኤም በማስተምርበት ትምህርት ቤት በአሁኑ ወቅት ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሠረት የሚያደርግ ጥናት ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ይህን ጥናት እንድታጠና ያነሳሳት ምክንያት በሴሚናር ኮርስ በከፊል ማሟያነት በተሰራው የጥናት ዳሰሳ ላይ በማዳመጥ ትምህርት ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ፅሑፎችን ስትዳስስ አልማዝ (2006)፣ እቴነሽ (1986) ፤ጥላሁን (2003) ሥራዎች ላይ ባደረገችው ዳሰሳ

የማዳመጥ ክህሎት ለማዳበር የቀረቡት ይዘቶች በክፍል ውስጥ የሚተገበሩበት ሁኔታ በአብዛኛው አለመታየቱ፣ ለማዳመጥ ክህሎት የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑን ተማሪዎች ማዳመጥን በተግባር በመለማመድ የሚማሩበት ሁኔታ አነስተኛ መሆኑን ለመመልከት ትላለች፡፡ ስለዚህ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑትም የማዳመጥ ክህሎት የክፍል ውስጥ አተገባበር ድክመት የተሰነዘሩ የጥናት ውጤቶች ሲሆኑ ይህ የትኩረት ማነስ በአሁኑ ወቅት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ነው፡፡ በማስተምርበት ትምርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የማዳመጥ ክህሎት ይዘት አተገባበር ትኩረት ያላገኘ ክህሎት እንደሆነና ተማሪዎችም ያዳመጡትን ጽሑፍ፤ ንግግር፤ ወይም ሀሳብ ተረድተዉ ያለችግር የመግለጽ ችሎታቸዉ በጣም አናሳ ወይም ምንም ሃሳብ የማይገልጹ መሆናቸዉን በልምድና ለረጅም ዓመት በማስተምርበት ግዜያት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ዉስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ተገንዝብያለሁ፡፡

በመሆኑም በዚህ መስክ የተለያዩ ጥናቶች ተካሄዷል፡፡ ለምሳሌ አልማዝ አለማየሁ (2006 ) በአዲስ አበባ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች፤ ጥላሁን ከበደ (2003) በአዲስ አበባ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነተ በሰሜን ወሎ፤ እቴነሽ ተገኝ (1986) በአዲስ አበባ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ አትኩሮ የተጠና ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ርዕስም "አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት ያደረገ እና የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግምገማ" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት መጠናት አለበት፡፡ ምክንያቱም ይህ ርዕስ ቀድሞውኑ ከተጠኑበት ቦታ የተለየ በመሆኑ፤ በ1ኛ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች መሠረታዊ የቋንቋ እዉቀት እንዲኖራቸዉ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ላይ ይህ ጥናት ቢጠና አስፈላጊ ነዉ ተብሎ ስለታመነበት ነዉ፡፡ ሌላዉ አሳሳቢ ችግር በማስተማር ልምድ በተረዳችዉ አብዛኛዎቹ መምህራን ለማዳመጥ ክሂል የሚመድቡት ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ተፈጥሮአዊ በሆነ ዉህደት እንደሚተገብሩት ባገኘቻቸዉ ልምድ ተገንዝባለች፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ማዕከል የሆኑት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይም ይህ ችግር በሰፊዉ የሚታይባቸው መሆኑን በማረጋገጧ ለዚህ ችግር መፍትሄ ካልተፈለገ ተማሪዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን በአግባቡ ለይተዉ የመረዳት ችሎታቸዉ ላይ የእዉቀት ዉስንነት ስላለባቸዉ የችግሩን አሳሳቢነት ያጎላል፡፡

ስለዚህ አጥኚዋ የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሆነዉን የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበር አናሳ በመሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ችሎታቸዉ በጣም ደካማ መሆኑን በማረጋገጧ የጥናቷን ዋና ኣላማ የማዳመጥ ክሂል አተገባበርን መመርመር ወይም መገምገም አስፈላጊ መሆኑን አግኝታለች፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዐቢይ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ነው፡፡ ይህ ጥናት በዐቢይ ዓላማ ላይ ተመርኩዞ ዝርዝር አላማዎችም አሉት፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች፡-

1. ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልዩነት አንፃር ይዘቶቹ በክፍል ውስጥ ክንውኖች እንዴት እየተተገበሩ እንደሆነ ለመፈተሽ፣
2. በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ብዙ የማዳመጥ ክህሎት ይዘቶች የአዳምጦ መረዳት አተገባበርን ጠብቀው መቅረባቸዉን ለመመርመር፣
3. ተማሪዎቹ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ እንደመሆናቸው መጠን ለማዳመጥ ክህሎት መማሪያ የቀረቡ ይዘቶች የተማሪዎቹን ፍላጎት መሠረት አድርገዉ የተመረጡ ናቸዉን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመፈለግ፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውኖች አተገባበር ግምገማ ሲሆን፤ ይህ ጥናት በትምህርት ቤታችንና በአካባቢዉ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክህሎት አተገባበር ላይ የሚታየዉን ችግር መፍትሄ የሚጠቁም በመሆኑ ይህ ጥናት ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ጠቀሜታዉም፡-

- የተማሪዎችን የማዳመጥ ክህሎት ብቃታቸዉን ለማሻሻል ይጠቅማል፣
- ተማሪዎቹ ለማዳመጥ ክህሎት መልካም አስተሳሰብ እንዲኖራቸዉና እንዲያዳብሩ ይጠቅማል፣
- በመማር ማስተማር ሂደት የማዳመጥ ክህሎት አተገባባር በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ሚዛናዊ ግንኙነት እንዲኖረዉ ጠቀሜታ ይኖረዋል፣
- መምህራን ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎችን በሚያስተምሯቸዉ ክፍሎች ለተማሪዎቹ አስፈላጊዉን ድጋፍ ለመስጠት ጠቀሜታ ይኖረዋል፣
- ተማሪዎቹም በዚህ ጥናት ያገኙትን ብልሃት በሌላ የትምህርት ዐይነት ዉስጥ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፣
- በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውኖች አተገባበርን መፈተሹ ለቀጣይ ማስተማሪያ ዝግጅት ጥቆማ ወይም ማሳያ ይሆናል፣
- ለወደፊት ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ አጥኚዎች እንደመነሻነት ለጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

በዚህ ርዕስ ላይ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ማለትም የፅሕፈት ክህሎት፤ የንግግር ክህሎት እና የማንበብ ክህሎት ትምርት ላይ ጥናት ማጥናት የሚቻል ቢሆንም ይህ ጥናት ግን በ1ኛ ደረጃ ኢ-አፍ-ፈት በሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበርን መገምገም ትኩረት ያደረገ ጥናት ሲሆን ሌሎች ክሂሎችን አያካትትም፡፡

ወሰነ ጥናቱም አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግምገማ በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚጠና ጥናት ነዉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የማዳመጥ ክሂል ምንነት

በማዳመጥ ክህሎት ምንነት ዙሪያ ብዙ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህ ምሁራን ውስጥ Underwood (1489:1) "ማዳመጥ በንግግር የተላላፈውን ሀሳብ ትርጉም አዘል በሆነ ሁኔታ ሀሳብን የማወቅ ወይም የመረዳት ሂደት ነው ሲሉ" ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም Grant (1989) "ማዳመጥ ከአንድ ንጥል ድምፅ ጀምሮ ውስብስብ መልዕክት እስከ መረዳት ድረስ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል፡፡" በመሆኑም ማዳመጥ በንግግር ሂደት ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያለውና በዓላማ የሚከናወን ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ ውስጥ በየጊዜው አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ክህሎት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ማዳመጥ ለሚደመጠው ነገር ትኩረት በመስጠት አውዳዊ ፍቺውን ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ እንዲሁም ተናጋሪዎች የተወሰኑ ቃላትን በተወሰኑ አገባቦችና አጋጣሚዎች ሲጠቀሙባቸው ምን ማለታቸው እንደሆነ መለየት መቻልም ነው Anderson and Lynchi, (1988 :1)::

ከላይ የተገለጸዉ ሀሳብ በማዳመጥ ሂደት አንድ በንግግር የተላለፈን ሃሳብ ትርጉሙን በመረዳት መልእክት ማስተላለፍ እንደሚቻልና ለሚደመጠዉ ነገር ትኩረት ሰጥቶ አዉዳዊ ፍቺን ማግኘት የሚቻል መሆኑን እንዲሁም በዓላማ የሚከናወን መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ሌላዉ የቀረቡት ብያኔዎች እንደሚያስረዱት አንድ ሰው የተነገረውን ወይም የተነበበውን ፅሑፍ አዳምጧል ለማለት የሚቻለዉ ከሚደመጠው ንግግር ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን መለየት፣ ሃሳቡን በቀላሉ መረዳት፣ እንዲሁም የተረዳውን ነገር ለሌሎች ማስተላለፍ መተርጎም ሲችል ነው የሚለዉን መረዳት ይቻላል፡፡

undrerwood (1989፡:7) የማዳመጥ ትምህርት በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን፣ ራስን ለማስተዋወቅ፣ መረጃ ለመለዋጥ፣ ስሜትን ለማጋራትና ራስን ለማዝናናት ጠቀሜታ እንዳለውና ክህሎቱም በትምህርት መዳበር እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡ ማረው (1998፡172) ማዳመጥ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ከማንኛውም የቋንቋ ክሂሎች

ይበልጥ በስፋት ያገለግላል። ይኸውም በአማካይ ከምንናገረው ሁለት እጥፍ ከምናነበው አራት እጥፍ፣ እንዲሁም ከምንፅፈው ስምንት እጥፍ የበለጠ እንደምናዳምጥ ያስረዳሉ።

በመሆኑም የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር የሚደመጥ ነገር ያስፈልጋል። የሚደመጠው ነገር ደግሞ በመቅረፀ ድምጽ (tape recorder) በመከማቸት፣ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችንና ምንባቦችን ማንበብ ወዘተ … ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ለማዳመጥ ትምህርት የሚቀርቡት ይዘቶች ንዑሳን ክሂሎቶችን ለማስተማር አቅም ያላቸው፣ ከገሃዱ ዓለም የሃሳብ ልውውጥ ጋር በአቀራረብ የሚመሳሰሉ፣ አጭርና ግልጽ የሆኑ እንዲሁም የዲስኩር ባህርያትን ያካተቱ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ገጠመኝና የክፍል ደረጃን ያገናዘቡ፣ ለውይይት የሚጋብዙና የሀሳብ ፍሰታቸው የተስተካከለ፣ በሚገባ የተቀነባበሩና የመረጃ እጦት (የሃሳብ ጉድለት) የማታይባቸው ሊሆኑ ይገባል።

Underwood (1994:1) ‹‹ማዳመጥ በንግገር የሚተላለፍ አንድን መልእክት ትኩረት በመስጠት የንግግሩን ፍሬ ነገር ወይም ሃሳብ ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነዉ›› በማለት ይገልጻሉ። karl (1996:189) በበኩላቸዉ‹‹ ማዳመጥ ማለት ሌሎች ሰዎች የተናገሩትን ነገር መለየትና መረዳት ማለት ነዉ›› ይላሉ። ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለዉ ማዳመጥ ማለት መልእክት ለመቀበል በትኩረት የምናከናዉነው ተግባር መሆኑንና የተማሪን ፍላጎት፣ ገጠመኙን እንዲሁም የክፍል ደረጃዉንም ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ያስረዳል።

Dunn (1998: 76) ስለ ማዳመጥ ሲያብራሩ፡- ማዳመጥ መስማት ማለት አይደለም። ማዳመጥ ነገሮችን ለይቶ ማወቅን፤ ማመሳከርን የሚይዝ ነዉ። አንድ ሰዉ ቋንቋ ለመማር መጀመሪያ በኅብረተሰቡ የሚነገረዉን ሥርዓተ ድምጽ እና ሥርዓተ ቃላት ማዳመጥ አለበት። በንግግርም ሆነ በዉይይት አንዱ የሌላዉን ንግግር በሚገባ ካላዳመጠ መግባባት ያዳግታል በማለት ገልጸዋል።

Rixon (1986፡3) በበኩላቸዉ ‹‹ማዳመጥ ማለት ለሚሰማ ጉዳይ ትኩረት በመስጠት የጉዳዩን ፍሬ ነገር የመረዳት ሂደት ነዉ›› በማለት ገልጸዋል። በድሉ (1996፡45) አገላለጽ ‹‹ማዳመጥ በአእምሮአችን ዉስጥ ንግግር ትርጉም የሚያገኝበት ዉስብስብ ሂደት ነዉ።››

ከላይ ከተገለጹት ሃሳቦች የምንረዳዉ ማዳመጥ ከመስማት የተለየና ትኩረት የሚሻዉ ተግባር መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም ማዳመጥ መልእክት የመቀበል፤ የመረዳትና የመተርጎም

ሂደት ሲሆን መስማት ግን አንድ ድምጽ ወደ ጆሮ መድረሱን በስሜት ህዋሳት አመካይነት የምንረዳበት ሂደት ነዉ፡፡

## 2.2 የማዳመጥ ትምህርት ምንድን ነው?

ማዳመጥ የመልዕክት ወደ ጆሮ መድረስ ሳይሆን የደረሰውን መልዕክት መረዳትና መተርጎምን የሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪውን ስለማዳመጥ የምናስተምረው የሚያዳምጠውን እንዲያደራጀው፣ እንዲረዳው፣ እንዲተረጉመው እና ምላሽ እንዲሰጥ በጥቅሉም በሀሳብ ልውውጡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ የማዳመጥ ትምህርት የሚባለውም ተማሪዎችን በዚህ መልክ የማዳመጥ ክህሎት ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡ Underwood (1989:4)፡፡

ይህን ሀሳብ Rixo (1983:1) ሲያጠናክሩት ‹‹የማዳመጥ ክህሎት በማኅበራዊ ሕይወትና ልምድ የሚገኝ ስለሆነ ትምህርት አያስፈልገውም›› ብለው የሚያምኑ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ጠቁመዋል፡፡

ማዳመጥ የመልዕክት ወደ ጆሮ መድረስ ሳይሆን የደረሰውን መልዕክት መረዳትና መተርጎምን የሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪውን ስለማዳመጥ የምናስተምረው የሚያዳምጠውን እንዲያደራጀው፣ እንዲረዳው፣ እንዲተርጉመው እና ምላሽ እንዲሰጥ ለማስቻል፣ በሐሳብ ልውውጡ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ የማዳመጥ ትምህርት የሚባለውም ተማሪዎችን በዚህ መልክ የማዳመጥ ክህሎትን ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር ነው underwood (1989:4)

Little wood (1981) በበኩላቸው ‹‹የማዳመጥ ትምህርት ተማሪውን በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ጠንካራ ተሳታፊ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ይህም ማለት መዋቅራዊ እና ማኅበራዊ የሆነውን አጠቃቀም እንዲለዩ ማድረግ ነው›› በማለት ይገልጻሉ፡፡፡

ከላይ ከተገለፁት ሀሳቦች እንደምንረዳው አንድ ሰው ለመማር በኅብረሰተቡ የሚነገረውን ሥርዓተ ድምፅ፣ ሥርዓተ ቃላት ማዳመጥ አለበት የሚለውን ሐሳብ ያስገነዝባል፡፡ Grant (1989:19-20) እንደገለፁት የማዳመጥ ትምህርት ተማሪዎች የተለያዩ ድምፆችን ለመለየት እንዲችሉ፣ የተለያዩ መልዕክቶችን በማዳመጥ ለመቀበል እንዲችሉ፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር የሚለማመዱበት ሂደት ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ በርካታ የዘርፉ ምሁራን እምነት፣

የዚህ ክህሎት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የተሰጠው አይደለም፡፡ ለአብነት ብንጠቅስ፣ Karl (1996:32) ‹‹በበርካታ አገሮች አዳምጦ መረዳት የተማሪዎች ችግር ነው›› ይላሉ፡፡

Ur (1984:9) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት የአፈፃፀም ሂደትን በተመለከተ በሚከተለው መንገድ ያብራራሉ፡፡

> *የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ሂደቶች (ክንውኖች) ተፈጥሯዊን የማዳመጥ ተግባራት የሚያሟሉ ናቸው፣ የማስተማሪያ መፅሐፍ ይዘቶችንም ከተለያዩ መፅሐፍትና ፅሑፎች የተለቃቀሙ ተማሪው ለምን እንደማያዳምጥ ምን እንደሚፈልግ ሳናውቅ የሚያዳምጧቸው፤ በማለት ገልፀዋል፡፡*

እንደ Underwood (1989:4) አመለካከትም ቀደም ባሉት ጊዜያት የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የሚያስፈልገው ተደርጎ አይቆጠርም ነበር፡፡ ማስተማር ማለት የመማር ሂደትን መደገፍ ነው ብለን ከተረዳንና የመምህሩ ሚና እንደረዳትነት ከወሰድነው የማዳመጥ ትምህርት አስፈላጊነትን እንረዳለን ይላሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንገነዘበው የማዳመጥ ትምህርት በዕለት ተዕለት ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ በተግባቦት ጊዜ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች የበለጠ የምንጠቀምበት ስለሆነ ትምህርት የማያስፈልገው ተደርጎ ቢቆጠርም እንደምሁራኑ ገለፃ ግን የመማር ሂደትን ለመደገፍ የማዳመጥ ትምህርትን በክፍል ውስጥ መተግበር ተገቢ እንደሆነ ነው የሚገልፁት፡፡

## 2.3 የማዳመጥ ክሂል የማስተማሪያ ዘመናዊ ዘዴዎች እና መመሪያዎች

ትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ ስኬትን ከፍ ለማድረግ በደንብ ማዳመጥ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እሱን ለማስተማር ምን ምን መመሪያዎች እንዳሉ ማወቅ ተገቢ ነዉ ፡፡ በዚህ ፅሑፍ ውስጥ የማዳመጥ ችሎታን ለማስተማር ሦስት ዋና ዋና መመሪያዎችና ሰባት ንዑሳን መመሪያዎችን በማቅረብ የማዳመጥ ግንዛቤን መገምገም እንደሚቻል ያስረዳል፡፡

### 2.3.1 መመሪያ አንድ፡- በቅድመ- ማዳመጥ ጊዜ

#### 1. ግብ ማዘጋጀት

ተማሪዎችን የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር መመሪያዎች ለእያንዳንዱ የአድማጭ እንቅስቃሴ ግብ ወይም ዓላማ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በመጀመሪያ ዓላማን በመግለጽ ይጀምራል፡፡ ይህ ለተማሪዎች ስኬት የት ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ መመሪያን ይሰጣቸዋል፡፡

#### 2. ዳራን መገምባት

በመቀጠል ተማሪዎች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ስላላቸው የግል ልምዳቸው ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሚያውቁትን በድምጽ ታሪኩ ውስጥ ከሚሰሙት ጋር እንዲያገናኙ መርዳት፡፡ ተማሪዎች ከማዳመጣቸዉ በፊት ምን መረዳት እንዳለባቸው ማብራራት፣ ኣዲስ ቃላትን አስቀድመው መመልከት፡፡ ስለ ቀድሞ እውቀት እንዲያስቡ፣ የታሪኩን ርዕሰ ጉዳይ እንዲገምቱ ወይም በሌላ መንገድ ለታሪኩ እንዲዘጋጁ መጋበዝ፡፡

#### 3. አካባቢውን ማዘጋጀት

ታሪኩን ጮክ ብሎ ለሁሉም በክፍል ዉስጥ ከመናገር መቆጠብ፣ በቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ በተቻለ መጠን ጸጥ በማድረግ ትኩረትን መገንባት፡፡ ለምሳሌ፡ - ተገቢ ከሆነ ለማዳመጥ የጆሮ ማዳመጫዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡

#### 4. የማዳመጥ ስልቶችን ማስተዋወቅ

በመቀጠል በተሳካ ሁኔታ ለማዳመጥ መሳሪያዎችንና ስልቶችን ማስተዋወቅ (ስልቶቹም ከዚህ በታች ቀርቧል)፡፡

### 2.3.2 መመሪያ ሁለት፡- በማዳመጥ ጊዜ

#### 5. ማስታወሻ-መውሰድ

ተማሪዎች ታሪኩን በሚያዳምጡበት ጊዜ በአስፈላጊ ሀሳቦችና ዝርዝሮች ላይ እንዲያተኩ ለመርዳት የማዳመጥ ማስተማሪያ መሳሪያን መጠቀም ይችላሉ፤ይህም ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- የማዳመጥ ማስተማሪያ መሳሪያ ቲ-ቻርቶችን፣ የቬን

ዲያግራሞችን፣ ወይም በታሪኩ ውስጥ የገጸ ባህሪን ድርጊት መከታተል እንዲችሉ ማድረግ ይችላሉ:: እንደነዚህ ያሉ ዝግጅቶች ተማሪዎችን ማዳመጥ ላይ እንዲያተኩሩና በሌሎች ሁኔታዎች ግንዛቤን እንዲረዱ ስልቶችን እንዲያስተምሯቸው ማስታወሻ እንዲይዙ ሊመሯቸዉ ይችላሉ::

### 6. የችግር አፈታት ስልቶችን ማብራራት

ተማሪዎች አንድን ቃል ወይም ሀሳብ ካልተረዱ፣ ከታሪኩ ውስጥ ፍንጭ ተጠቅመው ግምታቸውን ሊገልጹ ይችላሉ:: ራሳቸውን ችለው የሚያዳምጡ ከሆነ፣ ኦዲዮውን አቁመው እንደ አስፈላጊነቱ እንደገና ማሰብ ወይም ማዳመጥ ይችላሉ:: በዚህ ሂደት "ችግር ፈቺ አድማጮች"ሊሆኑ ይችላሉ:: ተማሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ በማስታወሻ ማዳመጥ ከመጀመራቸው በፊት እነዚህን ስልቶች መማር አለባቸው::

## 2.3.3 መመሪያ ሦስት፡ - (በድኅረ ማዳመጥ ጊዜ) ከማዳመጥ በኋላ

### 7. በድምጽ ታሪክ ላይ ማሰላሰል

በመጨረሻም፣ ቁልፍ ጭብጦችንና ቃላትን የመረዳት ግቦች ላይ በማተኮር ታሪኩን በማዳመጥ የተማሩትን በማቀናጀት ተማሪዎችን ማሳተፍ:: ለምሳሌ ተማሪዎች ለማዳመጥ የመረዳት ጥያቄዎችን በፅሑፍ እንዲመልሱና ምላሾቻቸውን እንዲያካፍሉ መጠየቅ :: ይህ ሂደት ከባልደረባ፣ ከትንሽ ቡድን ወይም ከጠቅላላው ክፍል ፊት ለፊት ሊሆን ይችላል:: በታሪኩ ውስጥ ቁልፍ ጭብጦች ላይ መወያየት እና ተማሪዎችን ከሌሎች ፅሑፎች ወይም ልምዶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጥሩ በማበረታታት ተማሪዎች ስለ ታሪኩ ጥያቄዎች በመፃፍ፣ በውይይት በመናገር፣ ራሳቸውን በመቅዳት ወይም በማጣመር ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ይቻላል:: Han Austin (2016)

## 2.4 ማዳመጥን የማስተማር አዳዲስ መንገዶች

ማዳመጥን ለማስተማር አዳዲስ መንገዶች እንዳሉ በጆናታን ማርክ ተጠቅሷል:: ማዳመጥን ለማስተማር አዳዲስ መንገዶችና ተግባራዊ ምክሮችን ጠቅሷል፡፡ አብዛኛዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ማዳመጥ በጣም አስቸጋሪ ችሎታ እንደሆነ አድርገዉ ይሰማቸዋል:: ተማሪዎቹ ወደ ፊት የሁለተኛ ቋንቋ አስተማሪ እንደመሆናቸዉ መጠን የማዳመጥ ትምህርትን

እንዴት እንደሚያስተምሩ የበለጠ ለማወቅ ይጓጓሉ፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት በብሪትሽ ካዉንስል በሚሰጡ አንዳንድ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮርሶች ላይ ማዳመጥን የማስተማር ዘዴ በጣም ያለፈበት ዘዴ አድርገዉ ያስቡ ነበር፡፡ ነገር ግን ሉዛንግ ማዳመጥን ለማስተማር አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዳሉና በመምህራን ማሰልጠኛ ኮርሶች ላይም ስለማዳመጥ ማስተማር እና ስለማዳመጥ አያያዝ የተስፋፋዉ በርካታ ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ሉዛንግ ይናገራሉ፡፡

እነዚህም ዘዴዎች፡- ብዙ የተቀረጹ መቅረጸ ድምጾችን መጠቀም፣ ትዕይንቶችን ማሳየት፣ ገጸ-ባህሪያትን ማስተዋወቅ፣ መዝገበ ቃላትንና ወዘተ… በመጠቀም የማዳመጥ ትምህርትን ለማስተማር ተማሪዎችን መዘጋጀት ነዉ፡፡

ሌላዉ ተማሪዎቹ ከማዳመጣቸዉ በፊት የአንቀጹን አጠቃላይ ቁም ነገር መረዳት እንዲችሉ የማዳመጥ ተግባራትን ማዘጋጀት፡፡ የዚህን ተግባር መልሶች መፈተሽ፤ አስፈላጊ ከሆነ የድምጽ ቀረጻዉን እንደገና ማስደመጥ፤ ተማሪዎችን ወደ በለጠ ዝርዝር ግንዛቤ የሚመራ ተጨማሪ ተግባራትን እንዲተገብሩ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ ቴፕ ሪከርድ ካለ እንደ አማራጭ መጠቀም ፡፡የድምጽ ቀረጻዉንና ተግባራቶቹን በተቻለ መጠን ትክክለኛ ማድረግ፡፡ ይሄዉም የተማሪዎቸችን የማዳመጥ ችሎታ እድገትን ለመደገፍ ተጽእኖ በማሳደር ረገድ በጣም አጋዥ ናቸዉ፡፡

ሌላዉ አማራጭ የተለያዩ የድመጽ ቅጂዎችን ወደ ክፍል ዉስጥ የማምጣት መንገድ ነዉ፡፡ ይሄዉም ወንድና ሴት፣ የተለያዩ እድሜ ያላቸዉ የተማሪ ዘዬዎች፣ የተለያዩ የድምጽ ጥራቶች፣ ንግግሮችንና ነጠላ ቃላትን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ቀረጻዎቹ በተለይ አድማጩ ከተናጋሪዉ ጋር የመገናኘት እድል በማይኖርበት ጊዜ ማዳመጥን ለማስተማር ወይም ለማለማመድ ተሰማሚ ናቸዉ፡፡ በማለት ገልጸዋል፡፡ Jhonathan Mark ( 2016 )

ከላይ ከቀረበዉ ሃሳብ መረዳት የሚቻለዉ ማዳመጥን ለማስተማር የተለያዩ መመሪያዎችንና ደረጃዎችን መሠረት ያደረገ ትመህርቱን ግልጽ ለማድረግ ፣ቁልፍ ጭብጦችን በመለየትና በመወያየት እንዲሁም የማዳመጥ ትምህርትን ለማስተማር አዳዲስ ዘዴዎችና መንገዶች እንዳሉ በመጥቀስ እንደዚሁም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የማዳመጥ ትምህርትን እንዴት እንደሚማሩ እና እንደሚረዱ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ትምህርቱን በቀላሉ መማር እንደ ሚቻል ያስገነዝባል፡፡

## 2.5 አዳምጦ የመረዳት ትምህርት ክንውን ደረጃዎች

የማዳመጥ ክህሎት በክፍል ውስጥ ሲቀርብ /ሲተገበር / ሦስት ደረጃዎችን ይከተላል፡፡ እነሱም ቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜ እና በድህረ ማዳመጥ የሚከወኑ የተለያዩ የክፍል ዉስጥ ተግባራትን እንደሚያጠቃልል በድሉ (1996)፣ underwood ( 1989 )፣ Snow and Nerkins፣(1983) ፣ and Rixon (1989 ) ይገልጻሉ:: ስለዚህ ሦስቱ ደረጃዎች ፡- የቅድመ-ማዳመጥ ደረጃ፣ የማዳመጥ ደረጃ እና የድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች ናቸዉ፡፡

### 2.5.1. ቅድመ-ማዳመጥ

በቅድመ-ማዳመጥ ደረጃ ተማሪዎችን ለማዳመጥ ማዘጋጀት ነው:: በሐሳብ ደረጃ፣ የማዳመጥ ሥራን አስቀድመው ማወቅ:: ከክፍል በፊት፣ የማዳመጥ ርዕስን ወይም ንግግርን ያዳምጡና እነዚህን ጥያቄዎች ያስቡባቸዉ፦ ሁኔታው ምንድን ነው? ስንት ሰው ነው የሚናገረው? ምን የተለየ ዘዬ ነው የሚሰሙት? ርዕሱ ምንድን ነው? ተማሪዎች ፈታኝ ሆነው ሊያገኟቸው የሚችሉትን የትኛውንም ቋንቋ ማስተዋል፡፡ (ቃላት፣ የላቀ ደረጃ መዝገበ ቃላት)? እንዲሁም ክፍል ከመጀመሩ በፊት፣ መሳሪያው በትክክል እየሠራ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ሲዲውን ወይም ኦዲዮውን መሞከር እንዲሁም ድምጹን መፈተሽ፡፡

ክፍል ውስጥ ሲሆኑ፣ተማሪዎች ኦዉዲዮ የሚያዳምጡ ከሆነ ኦዲዮዉን ከማዳመጣቸዉ በፊት ማድረግ የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ:: የማዳመጥ እንቅስቃሴን ማዋቀር፣፣ ለተማሪዎች የማዳመጥ ፅሑፍን ቀላል ቅድመ እይታ መስጠት፣ ትንሽ መረጃን ለመስጠት ከተፈለገ ግን ብዙ ሳይሆን በሀሳብ ደረጃ፣ ተማሪዎች ስለሚሰሙት ነገር እንዲያስቡት ማድረግ አለበት:: እንደ ርዕስ ወይም አጭር ዓረፍተ ነገር ያሉ ጥቂት መረጃዎችን መስጠትና የሚሰሙትን እንዲተነብዩ መፍቀድ፡፡

የኮርስ መፅሐፉን ገጽ አስቀድመው እንዲመለከቱ መጠየቅ:: ከማዳመጥ ርዕስ ጋር የሚሄድ የኮርስ መፅሐፍ ገጽ ካለ፣ ተማሪዎች ስዕሎቹን፣ ተግባራቶቹን፣ መመሪያዎችንና ጥያቄዎችን እንዲመለከቱ ጊዜ መስጠት:: ይህ ሁሉ ለተማሪው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል:: ያስታውሱ ተማሪዎቹ ምናልባት የማዳመጥ ርዕስን ከዚህ ቀደም አልሰሙምና በሁለተኛ ቋንቋ እያዳመጡ ነው::

Stiffen Brown "ሁልጊዜ የቅድመ -ማዳመጥ ሥራን" እንዲያዘጋጁ ይመክራሉ፡፡ ይሄዉም. ሁለት ዓይነት የቅድመ-ማዳመጥ ሥራዎችን ይጠቅሳሉ፡፡ የመጀመሪያዉ-ታች ላይ እና ሁለተኛዉ ላይ ታች፡፡ ታች ላይ ማዳመጥ የአድማጭ እይታን ለመረዳት በሰዋስው እና በቃላት ላይ ማተኮርን ያመለክታል ታች ላይ ያለው የቅድመ ማዳመጥ ተግባር ለአድማጭ ፅሑፍ ማዕከላዊ የሆኑትን መዝገበ ቃላት ወይም ሰዋሰው አስቀድሞ ማስተማር ይሆናል፡፡

ላይ ታች ማዳመጥ ደግሞ የአድማጭ ጽሑፍን ለመረዳት የቀደመ እውቀትን ወይም የፅሑፍ መዋቅር መጠቀምን ያመለክታል፣ ስለዚህ ላይ ታች ያለው የቅድመ ማዳመጥ እንቅስቃሴ ተማሪዎች ስለ ማዳመጥ ርዕስ የሚያውቁትን እንዲያስታውሱ መጠየቅን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡ - የማዳመጥ ርዕስ ቡና መሸጥ ከሆነ ፣ ሰዎች በቡና መሸጫ ውስጥ ምን እንደሚሉ እና እንደሚሠሩ ወይም በቡና መሸጫ ውስጥ ምን እንደሚመለከቱ ተማሪዎችን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ሊሰሙት ስላሰቡት የአድማጭ ፅሑፍ ዐይነት የሚያውቁትን መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ወይም፣ ምግብ ማብሰያው ምግብን እንዴት እንደሚሠራ የሚገልጽ ቪዲዮ ከሆነ፣ ምግብ ማብሰያው እያንዳንዱን የምግብ አዘገጃጀት መመሪያ ሲያብራራ (መጀመሪያ ፣ ከዚያ ፣ ከዚያ በኋላ) ምን ቃላት ሊመጡ እንደሚችሉ ተማሪዎች እንዲጠቁሙ መጠየቅ ፡፡

የቅድመ-ማዳመጥ ደረጃውን በትክክል አጭር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በአማካዩ አንዳንድ አስተማሪዎች ከአስር እስከ አስራ አምስት ደቂቃ የሚፈጀውን የቅድመ ማዳመጥ ሥራ እና የአንድ ደቂቃ የማዳመጥ ፅሑፍ ተከትሎ እንደሚያሳልፉ ተናግሯል፡፡ አንድ አጭር ተግባርን መምረጥ እና ረጅም ጊዜ እንዲወስድ አለማድረግ፡፡

በተጨማሪም ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከሚቀርበው ንግግር (ፅሑፍ) ጋር ትውውቅ የሚያደርጉበት ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎችን የቅድመ እውቀት ሊጠየቁ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለሚደመጠው ነገር እንዲገምቱ የሚደረግበት ደረጃ ነው፡፡ Underwood (1989) እንደሚገልጹት በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ፣ ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መመዘን፣ ተማሪዎች በትምህርቱ ዙሪያ ይነገራል ብለው የሚጠብቁትን ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ፣ ለትምህርት የቀረበውን ይዘት በተገቢው መልኩ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺን ለተማሪዎች ማሳወቅ፣ ከሚደመጠው

የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርጃ መሳሪያዎችን በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፣ በማዳመጥ ጊዜ ሊሠሯቸው የሚችሉትን ጥያቄዎችንና በማድመጥ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት መሠራት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል Underwood (1989)::

በመጨረሻም ከመስማታቸዉ በፊት የማዳመጥ ሥራን ማዘጋጀት፡ ሥራዉን በአፍ መፍቻ ቋንቋ በአጭሩ ማብራራትና አስፈላጊ ከሆነ በቦርዱ ላይ መጻፍ፡፡ ዙሪያዉን በፍጥነት መከታተልና ሁሉም ተማሪዎች በትክክለኛዉ ገጽ ላይ መሆናቸዉን ማረጋገጥ፡፡

በዚህ ደረጃ የምንረዳዉ ተማሪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያገኙበት ደረጃ እንደሆነ ፤ ከሚቀርበዉ ርዕስ ጋር ትዉዉቅ የሚያደርጉበት በዚህም ሂደት ሁለት ዐይነት የቅድመ ማዳመጥ ሥራዎችን የሚተገብሩበት ማለትም ከታች ወደ ላይ እና ላይ ታች ወደ ላይ ማዳመጥ የአድማጭ እይታን በመረዳት በሰዋሰዉና በቃላት ትምህርት ላይ ማትኮርና ስለ ሚያዳምጡት ርእሰ ጉደይ የሚገምቱበት ደረጃና እንደዚሁም አዳዲስ የቃላት ፍችን የሚረዱበትና የሚተነብዩበት የማዳመጥ ደረጃ መሆኑን ያስረዳል፡፡

## 2.5.2 የማዳመጥ ጊዜ

የማዳመጥ ደረጃ ተማሪዎች የሚያዳምጡበት እና አንድ ተግባር የሚያከናውኑበት ነው:: ማዳመጥ፣ ዋና ሃሳቦችን ማዳመጥ፣ ግምቶችን ማድረግ እና ማጠቃለያ የመሳሰሉ ተግባራትን ያሳያሉ:: አንድን ተግባር መመደብ ተማሪዎች እንዲያተኩሩ እና አስፈላጊ የቋንቋ ትምህርት ስልቶችን እንዲያዳብሩ ይረዳል::

ስለ አንዳንድ የተለመዱ የማዳመጥ ተግባራት ትንሽ ተጨማሪ መረጃ ለአጭር ጊዜ ማዳመጥ፡-

- ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት ማዳመጥ ማለት ነው፣ ስለዚህ ተማሪዎች የማዳመጥ ርዕስ ወይም ጭብጥ ለማግኘት መሞከር አለባቸው.፡፡
- የተለየ መረጃ ለማግኘት ማዳመጥ ማለት ነው፣ ለምሳሌ ገንዘቡ ምን ያህል ነበር? ወይም አውቶቡሱ ወዴት ይሄድ ነበር?

**ማመዛዘን**- ተማሪዎች በርዕሱ ላይ በግልጽ ያልተገለፀ መረጃ ለማግኘት የሚያዳምጡበት ቦታ ይህ ነው:: አንዳንድ ምሳሌዎች፡- ሁለቱ ሰዎች አንዳቸው ለሌላው ምን ይሰማቸዋል?

ወይም ሰውዬው ቀጥሎ ወዴት ይሄዳል ብለው ያስባሉ? በሐሳብ ደረጃ፣ መምህሩ የማዳመጥ ርዕሱን ወይም ምንባቡን 2 ወይም 3 ጊዜ ማስደመጥ አለበት፣ በእያንዳንዱ ጊዜ የተለየ ተግባር ማዘጋጀት፤ ብዙ ባለሙያዎች ሥራዎቹን ደረጃ እንዲሰጡ ይጠቁማሉ፡፡ ይሄዉም ከቀላል ወደ ከባድ፣ ለምሳሌ በአንድ ትልቅ ጥያቄ ከመጀመር፣ ከ3 እስከ 5 ዝርዝር ጥያቄዎችን መጠየቅ በመቀጠል፣ ከዚያም የማጣቀሻ ጥያቄን ማስከተል፡፡ እንዲሁም ለራስ አንድ ተግባር መስጠት ይገባል፡፡

ክፍሉን በመቆጣጠር. ትኩረት እየሰጡ የተበሳጨ የሚመስል ካለ በክፍሉ ውስጥ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ምንድነው? የሚሉትን ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የሚደመጠውን ርዕሰ ነገር በጥልቀት የሚያደምጡበትንና ተፈላጊ መረጃዎችን የሚሰበሰቡበት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚደመጠውን ፅሑፍ ወይም ንግግር በተመስጦ በመከታተል እና ማስታወሻ በመያዝ ልምምዱን በተገቢው ሁኔታ እንዲያከሂዱ የሚደረግበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን ተማሪዎች ስዕሎችን በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው እንዲያስቀምጡ፣ ያልተሟሉ መረጃዎችንና እቅዶችን እንዲያሟሉ፣ አንድን ፅሑፍ (ንግግር) እያዳመጡ ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንደሚችል እንዲገምቱ፣ የሚነገረውን ነገር በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ፣ አያያዥ ቃላትን ትኩረት ሰጥተው እንዲያደምጡ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ምክኒያቱም እንደዚህ ያሉ ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀሳቦች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ዝምድና ስለሚገልፁ ነው በድሉ (1996)፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የማስተማር መመሪያዎችና የማዳመጥ ደረጃዎች መልዕክት መረዳት የሚቻለዉ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር ምን ምን ሂደቶችንና መመሪያዎችን መከወን እንደሚገባ በዝርዝር የሚያስረዳና እንዲሁም የማዳመጥ ክንዉን ደረጃዎች ሥር በእያንዳንዱ የማዳመጥ ትምህርት ክንውን ሂደት በየደረጃዉ ምን ምን መተግበር እንደሚገባ እና አተገባበሩም ግልጽና ቀላል እንዲሆን፣ ተማሪዎችም የሚደመጠዉን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት ማዳመጥ እንደሚገባቸዉ፣ ፅሑፉን(ንግግሩን) እያዳመጡ ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንደሚችል የሚገምቱበት፣ የሚያዳምጡትን ርዕሰ ጉዳይ በቅደም ተከተል ማስታወሻ የሚይዙበት፣ እንዲሁም የቋንቋን ሥርዓትና ሰዋሰዉ ለመጠበቅ አያያዥ ቃላትንና ሥርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ትኩረት ሰጥተዉ የሚያዳምጡበት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

### 2.5.3. በድህረ-ማዳመጥ ጊዜ

ከማዳመጥ በኋላ ያለው ተግባር ከማዳመጥ ፅሑፍ በላይ የሚወስዷቸው እና ለተጨማሪ የቋንቋ ልምምድ ይጠቀሙበታል፡፡ በዚህ ጊዜ፣ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲመለከቱ እና ምን ለመረዳት እንደተቸገሩ እንዲመለከቱ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች በማዳመጥ ርዕስ ወይም ምንባብ ውስጥ ያለውን ቋንቋ እንደገና እንዲመለከቱ ጥሩ መንገድ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በሚያዳምጡበት ጊዜ ያልተረዷቸውን ቃላት እና ሀረጎች እንዲረዱ ሊረዳቸው ይችላል፡፡ እንዲሁም፣ ተማሪዎች በንግግር ቋንቋ እና በፅሑፍ ቋንቋ መካከል ያለውን አንዳንድ ልዩነቶችን እንዲያስተውሉ ሊረዳቸው ይችላል፡፡

የንግግር ተግባርን ማዘጋጀት ተማሪዎችን ተዛማጅ የንግግር እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መመደብ፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በአንድ ፓርቲ ውስጥ የሁለት ሰዎች ውይይት ከሰሙ፣ ውይይቱን በተለየ ሁኔታ እንዲደግሙት መጠየቅ ችግሮችን ፈልጎ ተማሪዎች በማዳመጥ ወቅት ምን ችግሮች እንደተፈጠሩ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ የትኞቹ ክፍሎች በጣም አስቸጋሪ ነበሩ? ግራ መጋባት ወይም አለመግባባት ያደረጋቸው ምንድን ነው? የሚሉትን ጉዳዮች የሚተገብሩበት ክፍል ነዉ፡፡

በድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ንግግር ወይም ፅሑፍ መሠረት በሃሰብ መስማማትና አለመስማማታቸውን ወይም ያዳመጡትን ከግላዊ ገጠመኝ (አስተያየት) ጋር በማዋሃድ ሊመልሷቸው የሚችሉትን ጥያቄዎች እንደተማሪዎቹ ማንነት በመጠየቅ የማዳመጥ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ደረጃ ነው Rixon (1986፣ 72) በሌላ በኩል Snow and Perkins (1979) እንደሚገልፁት ድህረ ማዳመጥ ተግባር ተማሪዎች የፈለጉትን ወይም የጠበቁትን መረጃ በትክክል ማግኘታቸውን ወይም አለማግኘታቸውን የሚያረጋግጡበት፣ የይዘቱን ርዕስ በጥልቀት ለመመርመርና የተናጋሪዎችን ዝንባሌ ለማወቅ የሚሞክሩበት ደረጃ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህሩ ምጋቤ ምላሽ (Feedback) በቃል መስጠት፣ ተማሪዎቹ በጥንድ በቡድንና በጋራ በመሆን የተሰጡትን መልሶች እንዲያመሳክሩ ማድረግ፣ በንግግሩ (በተደመጠው ፅሑፍ) ውስጥ ሊያከራክሩ የሚችሉ ነገሮችን በመምረጥ ተማሪዎቹ እንዲከራከሩ ማድረግ፣ ባዳመጡት ፅሑፍ ውስጥ የተሰማቸውን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፣ ወዘተ በዚህ ደረጃ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባሮች ናቸው Snow and Perkins (1979)፡፡

እንዲሁም ቋንቋን በማስተማር ሂደት ማዳመጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ በሌሎች ክሂሎቶች ውስጥ በአንድነት መገኘት አለበት የሚለው አመለካከት ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡ ይህ ማለት ግን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በማዳመጥ ላይ ያተኮረ ትምህርት ማቀድ አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ በአንድ ክህሎት ላይ ማተኮር ደግሞ ሌሎቹን ክሂሎቶች አለመንካት አይደለም Underwood (1989፣ 23):: ክሂሎቶችን ለማዳበር በሚቀርብ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎቶችን በተቀናጀ ሁኔታ የማዳበሩ አስፈላጊነት የተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ክህሎት የሚፈለገውን የችሎታ ደረጃ ለመወሰንና ትኩረት ለመስጠት ሲባል ክሂሎችን ነጣጥሎ ማቅረቡም ተቀባይነት አለው፡፡ የማዳመጥ ክህሎት በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ እንጂ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዳብሮ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተማሪው በየጊዜው በተለያዩ የማዳመጥ ሁኔታዎች ውስጥ በበቂ ሁኔታ መሳተፍ እንዲችል ክህሎቱን የሚያዳብሩ ልምምዶችን ማቅረብና በየጊዜው ክህሎቱን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማዳመጥ ክሂሎች ሙሉ በሙሉ ሊዳብር እንደማይችል በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማዳመጥ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ ጥናቶቹን በመከለስ Undersoon & Lynch እንዳሰፈሩት፡-

- ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት በሚጠቀሙበት ዘንድ እንኳን ቢሆን ክህሎት ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ ሊዳብር አይችልም፡፡ በአብዛኛው የዚህ ችግር ምክኒያቶች መረጃዎችን አዳምጦ የመረዳት ወይም መረጃዎችን ተርጉሞ የመጠቀም ክህሎት ናቸው Anderso &Lynch (1988፣60)፡፡

በአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን በሌሎች ያለውን የማዳመጥ ችግር በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ክህሎቱን ትኩረት ሰጥቶ በማስተማር ማስወገድ ይቻላል፡፡ አዳምጦ መረዳት ችሎታን መቶ ፐርሰንት ማድረስ ባይቻልም በማስተማር ለተማሪው አስፈላጊ የሆኑትንና ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸውን ችሎታዎች ማስጨበጥ ይቻላል Braown & Yule፣ 1983)፡፡

በዚህ ደረጃ ምንረዳዉ የማዳመጥ ክህሎት በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ ነው፡፡ ስለዚህ በአፍ መፍቻ ቋንቋም ቢሆን የማድመጥ ክህሎትን ለማዳበር ልምምዶችን ማዘጋጀትና ተማሪው ትኩረት ሰጥቶ እንዲለማመድባቸው የማድረጉ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም፡፡

## 2.6 የማዳመጥ ትምህርት አላማ

በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የማዳመጥ ትምህርት ዓላማ የሚተላለፈውን መልዕክት የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ከተለያዩ የማዳማጥ ባህሪያት ጋር ለማስተዋወቅ፣ ራስን ለማዝናናት፣ ንግግርን ለማድነቅ ወዘተ እንደሆነ ብዙ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በድሉ (1996፡46) under wood (1989:4) የማዳመጥ ትምህርት ዓላማዎችን ሲገልጹ እውቀትንና መረጃን ለማግኘት፣ ትዕዛዞችን ለመከታተል፣ የተገኘውን መረጃ ለመተርጎምና ለማገናዘብ፣ የተነገረውን ነገር ለመመርመር፣ ተናጋሪው የሚያራምደውን ሃሳብና ዝንባሌ ለመለየት፣ ጭብጥና ደጋፊ ሀሳቦችን ለማገናዘብ ወዘተ….. ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡

መስፍን (2000፡6) ‹‹የማዳማጥ ክህሎት የማስተማር ዋንኛ ዓላማ ተማሪዎች የማዳማጥ ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ለማስቻል መሞከር ነው፡፡›› በዚህ ደረጃ ሊሰመርበት የሚገባ ነገር ቢኖር የንባብ ልምድ የማዳመጥ ችሎታን ለማሳደግ እኩል የሆነ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው፡፡

አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስንመለከተው በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የማዳመጥ ትምህርት ዓላማ በሚከተሉት ነጥቦች ማካተት ይቻላል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች የማዳመጥ ትምህርት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ ተማሪዎች የሚያዳምጡትን ነገር ፍሬ ሐሳብ መጨበጥ እንዲችሉ ለመረዳት፣ ተማሪዎች ባዳመጡት ፍሬ ሃሳብ ላይ ተመርኩዘው በውይይት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ ተማሪዎች በተሳካ መልኩ በእውነተኛው ዓለም በማዳመጥ መግባባት እንዲችሉ ለመረዳት ነው በማለት በድሉ (1996፡46) እና under wood 1989 በዝርዝር ይገልጻሉ፡፡

## 2.7 የማዳመጥ ይዘት ምርጫ

የማዳመጥ ክህሎት በትምህርት ቤት የማስተማር ዋነኛ ዓላማ ተማሪው የሚሰማውን ነገር የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የመገምገምና የራሱን ምላሽ መስጠት የሚያስችለውን ክህሎት ለማስጨበጥ፣ በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና ሕብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የማዳመጥ ልምምዶችን በምናዘጋጅበት ጊዜ ተማሪዎች የሚጠቀሙበትን በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የማዳመጥ ሁኔታና ሊያጋጥማቸው የሚችሉ የማዳመጥ ችግሮችን ከግምት ማስገባት ይኖርብናል፡፡

Shir ፣ በተለያየ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ለማዳመጥ ትምህርት የሚሆኑ ይዘቶችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ትጠቁማለች። ተማሪዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚያጋጥመማቸው የማዳመጥ ሁኔታ እንዲለማመዱ ከተፈለገ ከነዚህ የማዳመጥ ሁኔታዎች ላይ የሚታዩ ዋና ዋና ባህርያት ያካተተ ልምምድ ሊቀርብላቸው ይገባል። ይኸውም በኅብረተሰቡ ውስጥ ስናዳምጥ፡-

1. የምናዳምጥበት ዓላማ ይኖረናል፣ ስለምናዳምጠው ነገር ይዘት አስቀድመን እንገምታለን፣
2. ለምንሰማው ነገር ወዲያውኑ ምላሽ እንሰጣለን፣
3. የምናዳምጠውን ሰው እናያለን፣
4. የምንሰማውን ነገር ትርጉም የሚጠቁሙ አንዳንድ አከባቢያዊ መገለጫዎችን ይኖራሉ፣
5. የሚሰማው ነገር አጠር አጠር ባሉ ምልልሶች የተከፋፈለ ይሆናል፣
6. አብዛኛው ምልልስ ያልታቀደ ምልልስ ነው። ስለዚህ ከመደበኛ ንግግር በድግግሞሽ፣ በንግግር ቋንቋነት ባህሪው፣ ንግግሩ በግልጽ እንዳይሰማ እንቅፋት በሚሆኑ ሁኔታዎችና በመደመጥ ባህሪው ይለያል Shyir፣ (1984፡ 3 — 10)።

የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር ይዘቶች ሲመረጡና የትምህርት ልምዶች ሲዘጋጁ ከላይ የተጠቀሱትን የማዳመጥ ሁኔታ ባህሪያት በተለያዩ አውዶች አካቶ በማቅረብ ተማሪውን በኅብረተሰቡ ውስጥ ከሚያጋጥሙት የማዳመጥ ሁኔታ ባህሪያት ጋር ማለማመድና በየማዳመጡ ሁኔታዎች ውስጥ በብቃት የሚያደምጥበትን ችሎታ ማስጨበጥ ይቻላል። ለተማሪዎች የሚቀርቡ የማዳመጥ ይዘቶች ተማሪውን በተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች የሚያለማምዱ መሆን ይኖርባቸዋል። ክህሎቱን በማዳበር ሂደት የትኛው የማዳመጥ ዓይነት ይበልጥ ሊተኮርበትና ብዙ ልምምድ ሊቀርብበት ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅን ይጠይቃል። ተማሪዎቹ ብዙ ጊዜ ሊገለገሉበት የሚያስፈልጋቸውን የማዳመጥ ዓይነት ለይቶ በማወቅ በዚያ ላይ የተመሠረተ ይዘት ማቅረብ ያስፈልጋል።

የማዳመጥን ክህሎት በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ሊቀርቡ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ለማበራዊ ምልልስ ማዳመጥና ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ናቸው Underson & Lynch: (1988) ፧ Richards፣ (1990) ፧ Rost፣ (1990)። ለማኅበራዊ ምልልስ ማዳመጥ ዓላማው በቋንቋ ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ የተናጋሪውን መልዕክት አቀራረብ መለየት ሲሆን በምልልሱ ተሳታፊዎች መካከል መግባባትን መፍጠር ላይ ያተኩራል። ለመረጃ መሻት ማዳመጥ ዐላማው አዲስ መረጃን ማግኘት ሳይሆን የሚተላለፈውን መልዕት በትክክል አዳምጦ መረዳት ላይ ያተኩራል።

በዚህ የማዳመጥ ዓይነት የሚቀርበው ነገር የትርጉም ግለኝነትና ቀጥተኛነት እንዲኖረው ይጠበቅበታል Richards፣ (1990)፡፡

የማዳመጥ ክህሎት በጥሩ ሁኔታ ሊዳብር የሚችለው አጠቃላይ አዳምጦ የመረዳት ችሎታንና ንዑሳን የማዳመጥ ክህሎቶችን የሚያለማምዱ ይዘቶች በተቀናጀ መልክ ሲቀርቡ ነው፡፡ ለተማሪው ሊቀርብለት ስለሚገቡ የማዳመጥ ንዑሳን ክህሎቶች በተመለከተ በርካታ ፀሐፍት የተለያዩ ዝርዝሮችን አመልክተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡ Harmer፡ (1983)፤ Liywuns Hil፡ (1986)፤ Rixon ፡(1986)፤ & Rost፡ (1990)፡፡ ይገኙበታል፡፡

- ከረጅም ንግግር ዐቢይ ሀሳብ ወይም ጭብጥ ማውጣት
- የንግግሩን ተከታታይ ክፍሎች አስቀድሞ መገመት
- ተጨባጭ እውነትና የግል አስተያየትን መለየት
- ተናጋሪው ሀሳብ ለማስተዋወቅ ርዕስን ለመቀየር ለትኩረት ነጥቦችን ለማብራራትና ለማስፋፋት፣ ተቃራኒ ሃሳቦችን ለመግለፅ የሚገለገልባቸውን ነጥቦች መገንዘብ፣
- ለተናጋሪው ተገቢውን መልስ ማዘጋጀት
- ተናጋሪው የሚሰጠውን መረጃና ስሜቱን መገንዘብ
- በንግግሩ ውስጥ የማይታወቅ ቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት
- የተናጋሪውን ዓላማ መረዳት
- የተደመጠውን ነገር ቀደም ብሎ ስለጉዳዩ ካለ እውቀት ጋር ማገናዘብ
- የተወሰኑ ዝርዝር ጉዳዮችን መረዳት
- በግልፅ የተነገሩ መረጃዎችን አዳምጠው መረዳት
- በግልፅ ያልተነገሩ መረጃዎችን ከአነጋገሩ መረዳት
- የማይጠቅሙ መረጃዎችንና ድግግሞሽ በመለየት አሳጥሮ ማቅረብ
- መረጃዎችን አዳምጠው ወደ ግራፍ፣ ሠንጠረዥ ወይም ካርታ መተርጎም
- ያዳመጡትን በራሳቸው አባባል ማቅረብ
- ከሚያደምጡት ውስጥ ፍሬ ሀሳቡን ለይተው ማስታወሻ መያዝ
- ከሚያደምጡት ውስጥ ምክኒያትና ውጤትን መለየት
- ስለሚደመጠው ነገር አጠቃላይ ግንዛቤ መውሰድ የሚሉት ፀሐፍት ከጠቆሚቸው የማዳመጥ ነዑሳን ክህሎቶች መካከል የሚገኙ ናቸው፡፡

በተማሪው ፍለጎትና ችሎታ ላይ ተመስርተው የሚመረጡት የመዳመጥ ንዑሳን ክህሎቶችን የሚመለከቱ ይዘቶች በንግግር ወይም በምንባብ አውዶች ውስጥ በማካተት ተማሪው ክህሎቱን እንዲያዳብርባቸው የሚያስችሉ ልምዶች ይቀርብባቸዋል፡፡

የማዳመጥ ክህሎት የሚዳብረው ልምምድ በማድረግ ነው፡፡ ተማሪው የሚደመጥ ነገር ስለቀረበለት ብቻ ያዳምጣል ማለት አይደለም፡፡ ላዳመጠው ነገር አንድ ዓይነት ምላሽ የቃል ወይም የተግባር መስጠት አለበት፡፡ አዳምጦ መረዳቱም ሊረጋገጥ የሚችለው በዚህ መንገድ ነው፡፡ ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር ተማሪውን ሊያሳትፍ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ለዚህም የማዳመጥን ክህሎት ለማዳበር በሚቀርቡ ይዘቶች ውስጥ ተማሪው አዳምጦ የሚፈጽማቸው ተግባራት ቢታቀዱ ጥሩ ነው፡፡ እንደ Shir አባባል የማዳመጥ ልምምዶች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት በተግባር ላይ ሲመሠረቱ ነው፡፡ ለተማሪው የሚቀርበው የማዳመጥ ተግባር፡-

- አስቀድሞ የታቀደ ዓላማ ያለው
- ተከታታይ የተማሪውን ተሳትፎ የሚጠይቅ
- ተማሪውን የሚያነቃቃ
- አንድ ዓይነት ውጤት የሚያስገኝ
- ተማሪው ሊያከናውነው የሚችለው
- ተማሪው በቃል ወይም በተግባር መልስ የሚሰጥበት መሆን አለበት Shir ፣ (1984 ፡ 25 — 29)፡፡

የማዳመጥን ክህሎት የሚያዳብሩ ልምምዶች ተማሪው የራሱን የማዳመጥ ዘዴ እንዲቀይስ የሚያለማምዱ መሆን አለበት፣ ይኖርባቸዋል፡፡ የማዳመጥ ዘዴዎች የሚደመጠውን ነገር በቀላልና በትክክል ለመረዳት የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው፡፡ የማዳመጥ ዘዴዎች በማኅበራዊ ምልልስ የማዳመጥ ሁኔታ ስላዳመጡት ጉዳይ ማብራሪያ ለመጠየቅና በትክክል ማዳመጥን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ሲሆኑ በመረጃ መሻት የማዳመጥ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ የተደመጠው መረጃ ቀደም ሲል በሚታወቀው የተለየና አዲስ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የምንጠቀምባቸው መንገዶች ናቸው Rost፣ (1990)፡፡

የማዳመጥ ዘዴዎች የማድመጥን ተግባር ቀላል እንዲሆን ይረዳሉ፡፡ ከማዳመጥ ሌላ በክፍል ውስጥ የማደመጥ ልምምዶች ሲካሄዱ ተማሪው የማዳመጥ ተግባሮችን በቀላሉ

እንዲያከናውኑ በቅደመ ማዳመጥ እያዳመጡና በድህረ ማዳመጥ የሚከናወኑ ተግባሮችን ከፋፍሎ ማቅረቡ ይረዳል፡፡ በዚህም መሠረት ለተማሪው የሚደመጠውን ነገር ከማቅረቡ በፊትቅድመ ማድመጥ መመሪያዎችን መስጠት፣ የሚደመጠውን ጉዳይ ርዕስ ማስተዋወቅ፣ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ያለቸውን የተወሰኑ መሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ በሚያደምጡበት ጊዜ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ማሳወቅ የመሳሰሉት ተማሪው በሚያዳምጥበት ወቅት ምን መፈጸመ እንዳለበት የትኛው መረጃ ላይ ማትኮር እንደሚገባው በአጠቃላይ የማዳመጥ ተግባሩን ግልፅ ስለሚያደርግለት በቀላሉ አዳምጦ መረዳት ይችላል፡፡ የማዳመጥ ይዘት ትምህርት ይዘቶች በቅድመ ማዳመጥ፣ እያዳመጡና ድህረ ማዳመጥ ተግባራት ተከፋፍሎ ሲቀርቡ ትምህርቱ የተቀላጠፈና ውጤታማ ይሆናል፡፡

ከዚህ ንዑስ ርዕስ መረዳት የሚቻለዉ የማዳመጥ ክህሎት በትምህርት ቤት የማስተማር ዋንኛ ዓላማ ያለዉና ተማሪዉ የሚያዳምጠዉን ነገር የመረዳት፣ የመተርጎም፣ መገምገምና የራሳቸዉን ምላሽ መስጠት የሚችሉበት ክህሎት መሆኑን፤ ሌላዉ የሚመረጠዉም የማዳመጥ ንዑሳን ክህሎት በተማሪዉ ፈላጎትና ችሎታ ላይ በመመስረት የሚዘጋጅና የሚመረጥ መሆኑን ነዉ፡፡

## 2.8. የማዳመጥ ይዘት ቅንብር

ማንኛውም ለትምህርት የሚቀርብ ይዘት ቅንብርን በተመለከተ ተከታታይነትን፣ ተጠባባቂነትንና አንድነትን ጠብቆ ከቀላል ወደ ከባድ፤ ከግልፅ ወደ ውስብስብ እያደገ በሚሄድ ቅደም ተከተል መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሠረት ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክህሎትን የሚያዳብሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ እየዳበሩ የሚሄዱ መሆን አለባቸው፡፡ Underson & Lynch ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ከሚያደርጉ ምክኒያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ ይላሉ ፡-

1. የሚደመጠው የቋንቋ ዓይነት
2. የሚደመጥበት ዓላማ ወይም ተግባር
3. የሚደመጥበት አውድ Underson & Lynch (1988 ፡ 46)

የማዳመጥ ትምህርት ይዘት አቅርቦትን በተመለከተ "ተማሪዎች በጣም ከባድና ውስብስብ ወደሆነ ልምምድ ከመግባታቸው በፊት ቀላል በሆነ ልምምዶች ጥሩ ውጤት ማምጣትና

መበረታታት ይኖርባቸዋል ይላሉ Underso & Lynch (1988 ፡ 44)፡፡ የሚደመጠውን ነገር የግልፅነት ደረጃና የይዘት ዓይነት ያመለክታል፡፡ የሚደመጠው የቋንቋ ዓይነት አዳምጦ የመረዳት ሁኔታን ከባድ ወይም ቀላል ያደርጋል፡፡

በማዳመጥ የሚፈፀሙ ተግባሮች ባህሪ ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ያደርገዋል ሲባል፣ የተለያዩ የማዳመጥ ተግባሮች ለተማሪው የተለያዩ የክብደት ደረጃ ያላቸውን ልምዶች ይዘው እንደሚቀረቡ ያሳያል፡ ለምሳሌ ወዲያውኑ ምላሽ የሚሹ ተግባሮች አዳምጦ መመለስ ወይም በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ካዳመጡ በኋላ ተፈላጊውን መረጃ መርጦ ከሚፈፅሙ ተግባሮች ምሳሌ ዋናውን ሀሳብ አሳጥሮ ማቅረብ ቀላል ናቸው፡፡ እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ አስተያየቶች መካከል ያለው ልዩነት መገንዘብ ከሚጠይቅ የሚደመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው፡፡ የሚደመጥበት አውድ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል፡፡ የሚደመጠው ጉዳይ መረጃ ብዛትና የማዳመጥ ሂደት የሚፈጀው ጊዜ ናቸው፡፡ ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ሊያደርጉ የሚችሉ፤ ምክኒያቶችን ስንመረምር በይበልጥ ማተኮር ያለብን በሚደመጡ ጉዳዮች የቋንቋ አቅርቦት ባህሪና በማዳመጥ የሚፈፀሙ ተግባሮች ባህሪ የክብደት ደረጃ ላይ ነው በማለት አበክረው ያሳስባሉ Underson & Lynch (1988)፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ የሚያሰኙ ምክኒያቶችን እንደ መመዘኛ በመጠቀም ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክህሎትን የሚያዳብሩ ይዘቶች የክብደት ደረጃውን የጠበቁና ከተማሪው ችሎታ ጋር የሚመጣጠኑ አድርጎ መምረጥና ማቀናበር ይቻላል፡፡

## 2.9 የማዳመጥ ክሂል ማስተማርያ መሳሪያዎች

Underwod (1989) እንደሚገልጹት የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር ከሚረዱ ነገሮች መካከል የተቀረጹ ካሴቶች፣ ቀጥተኛ የትምህርት ገለጻዎች፣ የሥነፅሑፍ ሥራዎች፡ የምስል ቁሶች ፡ ቃለ ምልልሶች እና የስልክ ላይ ንግግሮች ይጠቀሳሉ፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ የሚደረጉ ንግግሮችን እንዲያዳምጡና ካዳመጡት ነገር ተነስተዉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናወኑ በማድረግ ክህሎቱን ማስተማር ይቻላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ መሳሪያዎች የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር ፋይዳዉ የላቀ መሆኑን ምሁሩ ይገልጻሉ፡፡

## 2.9.1 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለጻዎች

እንግዶችን ወደ ክፍል በመጋበዝ ወይም ተናጋሪዉ ወደሚገኝበት አካባቢ በመዉሰድ እንዲያዳምጡ የሚደረግበት ሂደት ነዉ፡፡ የዚህ ዐይነቱ ስልት ለተማሪዎቹ ቀጥተኛዉን ቃላዊ ገለጻ ስለሚያቀርብ በርካታ ጥቅሞች ይኖሩታል Underwood (1994 ፤ 77)፡፡ ከእነዚህ ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹን ብንመለከት፡- በሚያዳምጡበት ጊዜ ልዩ ልዩ የድምጽ ቅላጼዎችንና የፍጥነት ደረጃዎችን ማስገንዘብ፡ ከሚቀርቡ ንግግሮች ተማሪዎች የንግግር አቅራቢዉን ማንነት፣ እድሜ፣ ስሜት፣ አካላዊ ገለጻ ወዘተ… በመገንዘብ ሲረዱና ለቀረቡላቸዉ ጥያቄዎች ምክንያታዊ የሆነ ምላሽ እንዲሰጡ ማስቻል ተናጋሪዉ አድማጮች ሊያዳምጡት በሚችሉት መጠን ስለሚናገር የተማሪዎችን የማዳመጥ ክህሎት ለማዳበር ተመራጭ መሆኑ ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡

## 2.9.2 በመቅረጸ ድምጽ የተዘጋጁ

የተቀረጹ ማስተማር መሳሪያዎችን ለማዳመጥ ክህሎት ማስተማሪያነት መጠቀም ያለዉ ጠቀሜታ የጎላ በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመቅረጸ ድምጽ ሆነ በተንቀሳቃሽ ምስል የተቀረጹ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማስተማሪያነት መምረጡ ብዙ ጥቅም አለዉ Underwood (1994); Rixon (1990;11) :: በማለት ገልጸዋል፡፡

እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀምን በተመለከተ Underwood (1994;94)፡፡እንደሚያብራሩት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቀረጹ ድምጾችን ወደ ክፍል በማምጣት ማስተማር እየተለመደ መጥቷል፡፡ ነገር ግን ዋናዉ ነገር እነዚህን የተቀረጹ ድምጾች መጀመሪያዉኑ ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር አብረዉ የተዘጋጁ መሆን ኣለባቸዉ፡፡ የተቀረጸዉ ካሴት በክፍል ዉስጥ በሚሰማበት ጊዜ ተማሪዎቹ መማሪያ መፅሐፎቻቸዉ ላይ ሆነ ተብልዉ የተዘጋጁ ክንዉኖችን እንዲሠሩ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡ በክፍል ከቀረበዉ ማዳመጥን በተቀረጹ ድምጾች የማስተማሪያ መሳሪያ በተጨማሪ እንደ Underwood (1994 ፤ 90)፡፡ አገላለጽ ከተቻለ ቪዲዮንም ለማዳመጥ ማስተማሪያነት መጠቀም ይቻላል፡፡ በእንዲህ ዐይነቱ መሳሪያ ማዳመጥን ማስተማር በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ጥቅሞች መካከል አንዱ ተማሪዎች የተናጋሪዉን መልዕክት እስከ ንበቱ በመከታተል መግለጽ ስለሚችሉ ነዉ፡፡

በተጨማሪም Rixson (1990፤11) እንደገለጹት ለምሳሌ የተቀረጹ ስፖርታዊ ዉድድሮችን ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች እንዲያዳምጡ ቢደረግ ዉጤቱን ለመስማት

ይጓጓሉ፤ እንዲሁም ከጓደኞቻቸዉ ጋር ማዉራትን ይሻሉ፤ ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ ይገምታሉ፤ ማን ጎል እንዳስቆጠረ ማዳመጥ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ሂደት ዉስጥ ሁሉ ንቁ የማዳመጥ ትምህርት ይካሄዳል፡፡ በዚህም የማዳመጥ ክህሎትን ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡

### 2.9.3 በስእል፤ ካርታ ፤ሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁ

ለተማሪዎች የተመረጡት ይዘቶችና ርዕሰ ነገሮች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ልምምድ ጋር የሚሄዱ ከሆነ በምስል አስደግፎ ማዳመጥን ማስተማር የተሸለ እንደሆነ Underwood (1994፤104)፡፡ ገልጸዋል፡፡ እንደ Underwood (1994፤104)አገላለጽ ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር በመማሪያ መፅሐፎቻቸዉ ዉስጥ በተለያየ መልኩ ማዳመጥን ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶች ወይም ሌሎች ተጨማሪ ይዘቶችን በምስል በማስደገፍ ትምህርቱን መስጠት ተማሪዎቹ በጥንቃቄ እንዲከታተሉና የሚጠየቁትንም ጥያቄ በአግባቡ እንዲመልሱ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ማዳመጥን ለማስተማር ሊያገለግሉ የሚችሉ ምስሎች ወይም መርጃ መሳሪያዎች ካርታ፣ ስዕላ ስዕል ፤ ሰንጠረዥ ወዘተ… የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ስለዚህ የማዳመጥ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ታስበዉ የተዘጋጁ ይዘቶችና ክንዉኖች በዚህ መልክ ማዘጋጀቱና አለመዘጋጀቱን መማሪያ መፅሐፎች በሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ በዚህ አንጻር ቢፈተሽ መልካም ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ባለዉ መልኩም ማዳመጥን በተቀረጹ የቪዲዮ ምስሎች ለማስተማር ቢሞከር ዉጤታማ እንደሚሆን የታመናል፡፡ Underwood (1994፤104- 108)፡፡

### 2.9.4 ሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎች

በሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋን ማስተር ተማሪዎች በእዉነተኛ አዉድ ላይ የተመሰረተ የተለያዩ አገባቦችን እንዲያጠኑ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በእዉነተኛ አዉዳቸዉ እንዲገኙ፤ የአመለካከት መገለጫን እንዲለኩ እና ተጨባጭ በሆነ የሰዎች ሕይወት አዉድነት ቋንቋን እንዲማሩ ያስችላል በድሉ (1996፤ 3-4)፡፡

Harmer (2001፤213) እንደ ገለጹት ለተማሪዎች አጫጭር ታሪኮችን (ልቦለዶችን) በክፍል ዉስጥ በማቅረብ የማዳመጥ ክህሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ሥራዎችን ለመስተማሪያነት ስንመርጥ ተማሪዎች በሚነበብላቸዉ የሥነ-ፅሑፍ

ሥራ ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ገጸ-ባህሪያትን ይለያሉ፤ የተሰማቸዉን አስተያየት ይሰጣሉ፤ እያዳመጡ ማስታወሻ በመያዝ ታሪኩ ወዴት እየሄደና ፍጻሜዉን ጭምር ይተነብያሉ፡፡

Andersoon & Lynch (1991፤18) ይህን ሃሳብ በመደገፍ ማዳመጥን ለማስተማር በሚያመች መልኩ አጫጭር ፅሑፎች በመማሪያ ክፍል ዉስጥ ቢያቀርቡ መልካም እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች የምንገነዘበዉ የተለያዩ የማዳመጥ ክህሎት ማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዳሉና እነዚህን መሳሪያዎች ተጠቅመን ስናስተምር ዉጤታማነቱ የጎላ መሆኑንና በተይ በሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎች በምናስተምርበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን እንደሚለመዱ፤ እንዲሁም ሥነፅሑፋዊ ሥራዎች የተለያዩ ማኅበራዊ አዉዶችን መሠረት አደርገዉ ስለሚዘጋጁና ሳቢነትም ስላላቸዉ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር እንደሚጠቅም መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.10 የማዳመጥ ንዑሳን ክህሎት

የማዳመጥ ክህሎት በጥሩ ሁኔታ ሊዳብር የሚችለው ንዑሳን የማዳመጥ ክሂሎችን የሚያለማምዱ ይዘቶች በተቀናጀ መልክ በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ነው፡፡ ለተማሪዎች ሊቀርቡላቸውስለሚገቡ የማዳመጥ ክህሎትን በተመለከተ በርካታ ፀሐፊያን የተለያዩ ዝርዝሮችን አመልክተዋል (Hrmer 1991: Rost 1990, Ur 1984)::

እንደ Ur (1984:25-29) አመለካከት በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ተመርኩዘው የሚመርጡ የማዳመጥ ንዑሳን ክሂሎችን እንዲያዳብሯቸው የሚያስችሉ ልምምዶች በክፍል ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የማዳመጥ ክህሎት የሚዳብረው ልምምድ በማድረግ ነው፡፡ ተማሪው የማዳመጥ ነገር ሲቀርብለት ብቻ ያዳምጣል ማለት አይቻልም ላዳመጠው ነገር አንድ አይነት ምላሽ የቃል ወይም የተግባር መስጠት አለበት፡፡ አዳምጦ መረዳቱን ሊያረጋግጥ የሚችለው በዚህ መንገድ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

Harmer 1991 እንደገለጹት የማዳመጥ ልምምዶች የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው በተግባር ላይ ሲመሠረት ነው፡፡ ተማሪዎችን ለማለማመድ በተግባር ላይ የሚውሉ ንዑሳን የማዳመጥ ክሂሎችም ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 2.10.1 ፍሬ ሀሳብ (ጭምቅ ሀሳብን) ማውጣት

ፍሬ ሀሳብ የምንለውመ የንግግሩ የተጨመቀ ሀሳብ ነው። ይህም ንግግሩ ከተደረገበት ዐውድ፣ በተናጋሪው እንቅስቃሴ እና አካላዊ ሁኔታ፣ ከድምፀቱ እንዲሁም ከቃላቱ አጠቃቀሙ እና ከዓረፍተ ነገሩ አወቃቀር በአጠቃላይ የምንደርስበት ጭምቅ ሀሳብ ማለት ነው በ Anderson and lynch (1983)፤ under wood (1989፡ 22-23) ።

እንደ Harmer (1991) ገለፃ ፍሬ ሃሳቡን ለመረዳት መቻል የሚለው ክህሎት የሚዳብርው ፅሑፎችን አስደምጦ ፍሬ ሃሳቡን የሚጠይቁ መልመጃዎችን በማዘጋጀት ነው።

### 2.10.2 አውዱን መለየት

ዐውዱን መለየት የምንለው ንግገሩ በምን ወቅት ወይም ሁኔታ እንደተነገረ የሚገነዘቡበት ነው። አንድ አድማጭ በንግግር ወቅት የተሟላ ግንዛቤ የሚያገኘው በቃላቱ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ባሉ ሁኔታዎች ጭምር ነው። በመሆኑም የሚያዳምጠውን ነገር መልዕክት ለመረዳት አውዱንም መለየት ያስፈላጋል። አንድን ንግግር በትክክል ለመረዳት በዚያ ንግግር ውስጥ የተለየ ቃል በአንድ የተለየ ሁኔታ መኖሩን ከዐውዱ መረዳት ይቻላል under wood (1989፡1-4) ስለዚህ ተማሪዎች አንዱ ሊያዳብሩት የሚገባ ክህሎት የማያውቁትን ቃል (ሀረግ) ፍቺ በአውድ አማካይነት መረዳት ነው። ለዚህም በቂ ልምምድ ሊሰጣቸው ይገባል።

### 2.10.3 ተዛማጅ ሀሳቦችን በየፈረጃቸው ማደራጀት

ተዛማጅ ሃሳቦችን በየፈረጃቸው ማደራጀት ማለት እንደ በድሉ (1996፡49) ገለፃ በአንድ ምድብ ሥር የሚካተቱ ሃሳቦችን በመለየት እንደተስማሚነታቸው ማደራጀት ማለት ነው። ይህም አዳምጦ ለመረዳት ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው። ምክንያቱም ሁል ጊዜ ሁሉን ነገር በንጥልነት መረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን ዝርዝር ነገሮች በተወሰኑ ምድቦች ለይቶ ማየቱ ነገሮችን ለመረዳት ቀላል እንዲሆን ያደርጋል።

### 2.10.4. መረጃ ለመፈለግ (ለማግኘት)

መረጃ ለመፈገል ማዳመጥ አላማው አዲስ መረጃ ማግኘት ሲሆን የሚተላለፈውን መልዕክት በትክክል አዳምጦ መረዳት ላይ ያተኩራል። በዚህ የማዳመጥ ተግባር የሚቀርበው ነገር ትርጉም ግልፅነትና ቀጥተኝነት እንዲኖረው ይጠበቃል Richards (1985:1999)::

### 2.10.5 ዝርዝር መረጃን መረዳት

ዝርዝር መረጃን መረዳት የሚባለው አድማጭ በአንድ ንግግር ዐውድ ውስጥ ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች በሚቀርብበት ጊዜ የቀረቡትን ነጥቦች መለየት ሲችል ነው፡፡ በዚህ መልክ አልፎ አልፎ በንግግር ወቅት ብዙ ዝርዝር ጉዳዮች ሲነሱና እነዚህን መረጃዎች መጨበጥ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስለ አንድ ነገር ዝርዝር መግለጫ በመስጠት አጠቃላይ ገፅታውን እንድንረዳ የሚደረግበት አቀራረብ ሊኖረው ይችላል፡፡ ዝርዝር መረጃ መረዳት የሚባለውም ይህ ነው በድሉ (1996፡49) Anderson and lynch (1983) በማረዉ (2003፣134) አገላለፅ የሚፈለገው መረጃ በዐይነት ብዙ ሊሆን ይችላል፡፡ ተናገሪው በቀጥታ ለማለት የፈለገው ምንድነው? ስንት? ለምን? ምን ያህል ጊዜ ወዘተ...ዐይነት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት ዝርዝር መረጃዎችን በማጣቀስ ነው፡፡

### 2.10.6 አጠቃላይ መረጃ (ግንዛቤ) ለማግኘት

እንደ Harmer (1991) ገለፃ ስለምናዳምጠው ነገር ጥቅል ግንዛቤ ለማግኘት ስንል ልናዳምጠው እንችላለን፡፡ በዚህ ሂደት ለሚፈለገው አጠቃላይ መረጃ (ዋና ጉዳይ) አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ያልሆኑትን ጉዳዮች ከግምት ማስገባት ወይም በእነዚህ ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ አስፈላጊ ድግግሞሾች፣ ዝርዝር ጉዳዮችንና አገላለፆች ላይ ጊዜ አለማጥፋት ይመረጣል፡፡ የንግግሩ ዋና ጉዳይ ብቻ ለማግኘት ሲባል ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ባለመስጠት ማዳመጥ ይቻላል፡፡

### 2.10.7 መገመት መቻል

ብቃት ያላቸው አድማጮች በርዕሱ ላይ ካላቸው እውቀትና ልምድ በመነሳት ወይም ማብራሪያውን ገልፅ ለማድረግ ከቀረቡት ስዕሎች፣ ካርታዎች፣ ዲያግራሞች፣ ቻርቶችና የመሳሰሉት ላይ በመመርኮዝ ነገሩን ከማዳመጣቸው በፊት ቀድመው የመገመት ችሎታን ለማዳበር አብዛኛውን ጊዜ የሚከናወኑ ሁለት ተግባራት አሉ፡፡ እነሱም ቅድም ማዳመጥና የማዳመጥ ጊዜ ሂደቶች ናቸው፡፡ ቅድመ ማዳመጥ ርዕስ ነገሩን ከተዋወቁ በኃላ ምን ምን ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ በመጠየቅ ይከናወናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በዚህ ርዕስ ምን ቁምነገር ይነሳል ብላችሁ ትገምታላችሁ? በሚል ሊጠየቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም በማዳመጥ ሂደት ከፅሁፍ

የተወሰኑ ክፍሎች ካነበቡ በኋላ ቀጥሎ ሊነገር የሚችለውን ነገር በመጠየቅ ሊከናወን ይችላል፡፡ ማገረው (2002፡133)

### 2.10.8 የሀሳብ አደረጃጀትን መረዳት

አንድ ሰው በሚያዳምጥበት ጊዜ ሀሳብ ወይም ሐረግ በምሳሌ ወይም በአስረጅ መደገፍ ነበረበት›› የሚል አስተያየት ሊሰጥ ይችላል፡፡ በመሆኑም የንግግሩን አደረጃጀትና አወቃቀር ለመረዳት የአያያዥ ሚና መረዳት ያስፈልጋሉ፡፡ የአንቀፃችን አደረጃጀት እንዲሁም የግጥምጥምነት መመስረቻ መሳሪያዎችን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎችን ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑ እነዚህን ብልሀቶች ማለማመድ ብሎም መረዳት ይኖርባቸዋል ማገረው (2003፡ 134)

ከላይ የተገለፀው ሐሳብ የማዳመጥ ክህሎት ማስተማሪያ ይዘት ሥር የተለያየ የማዳመጥ ንዑሳን ክህሎት እንዳሉና በእነዚህ ንዑሳን ሥር ዝርዝር የሆኑ የማዳመጥ ማስተማሪያ ይዘቶችንና ብልሀቶችን ያካተቱና እነዚህን ንዑሳን ክህሎቶች በአግባቡ በመጠቀም የማዳመጥ ትምህርት በማስተማር ተማሪዎችን ውጤታማ እንደሚያደርግና ጥሩ አድማጭ እንደሚሆኑ ያስረዳል፡፡

## 2.11 ጥሩና ተደጋጋሚ ማዳመጥ በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ

ጥሩ ማዳመጥ በተናጋሪው የተሰጡ ሁሉንም መረጃዎች በትኩረት መከታተልን ያካትታል፡፡ ቃላትን ብቻ ሳይሆን የቃል ያልሆኑ ምልክቶችንም ጨምሮ የድምፅ መገለጫዎች፣ ምልክቶችና የሰውነት ቋንቋዎች ጥሩ ማዳመጥና እንደሚከታተሉት እና ሌላውን ለመረዳት መሞከርን ያሳያል፡፡ አንድ ሰው የቃሉ ልምድ ለዚህ ንቁ ሂደት አድማጮችን መናገርም ያካትታል፡፡ ጥሩ አድማጭ ለመሆን መጀመሪያ የራስን ዋና እቅድ እና ግብን ለመለየት ራሳችንን ለማዳመጥ ትንሽ ጊዜ መውሰድ አለብን፡፡ ይህ ደግሞ ሌሎችን ለመረዳት በሚፈልጉበት ጊዜ አስፈላጊ መነሻ የሆነውን የት እንዲቆሙ የማወቅ መሠረት የመሆን ስሜት ይሰጣል፡፡

**ርህራሄና ግንዛቤ፡-** ቀጣዩ ደረጃ ሌሎችን ማዳመጥ ሌላውን ማወቅ ነው፡፡

**የአንድ ሰው እቅድና ግብ፡-** ይህ የጋራ መግባባትን ለማግኘትና ለማቆየት ያስችላል፡፡

**ፍሬያማ ግንኙነቶች፡-** ይህ ስሜታዊነት ያለው ማዳመጥ ውጤታማ ግንኙነት ለመፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በተጨባጭ የሚስማማው ነጥብ ለተናጋሪው የመስማት ኃይልን ያጎላል፡፡ በተለመደው በሜካኒካል ምላሾች ውስጥ ማለፍ ሳይሆን ምን እንደሚሰሟቸው ማዳመጥ፡፡ በስሜታዊነት ለማዳመጥና ለማለማመድ ጊዜ ይወስዳል፡፡

በአጠቃላይ የተለያዩ ምሁራን ስለማዳመጥ ምንነት የተለያየ ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም በማድመጥ ምንነት ክፍል ውስጥ ማዳመጥ በንግግር የተለላፈውን ሀሳብ ትርጉም አዘል በሆነ ሁኔታ ሀሳቡን የመረዳት እንደሆነ ለሚደመጠው ነገር ትኩረት በመስጠት አውዳዊ ፍቺን ለማግኘት፣ ማዳመጥ በሦስት ደረጃዎች የተከፋፈለና በእያንዳዱ ደረጃ ሥር አገለግሎቱንም ግልፅ የሆነ ዝርዝር ሀሳብ ተሰጥቷል፤ በተጨማሪዎች ባዳመጡት ፅሑፍ ውስጥ የተሰማቸውን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፣ በዚህ ደረጃ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባሮችን እንዲተገብሩ የሚደረግበት ሁኔታ የተገለፀበት፣ እንዲሁም ቋንቋ በማስተማር ሂደት ማዳመጥ ከፍተኛ ደረጃ እንዳለውና በሌሎች ክህሎት ውስጥ በአንድነት መገኘት እንዳለበትና ተቀባይነትም እንዳገኘ የማዳመጥ ክህሎት በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ እንጂ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዳብሮ የሚያበቃ አለመሆኑ የማዳመጥ ክህሎት ይዘቶች ሲመረጡና ሲዘጋጁ ለተማሪዎቹ የሚቀርቡ የማዳመጥ ይዘቶች ተማሪውን በተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች የሚያለማምዱ መሆን ያለበት መሆኑ እና የማዳመጥን ክህሎት በሚያዳብሩ ይዘቶች ውስጥ የተለያዩ የማዳመጥ ዓይነቶች ዋና ዋናዎቹ ለማኅበራዊ ምልልስ ማዳመጥ ችሎታን የመገምገምና የመምከር ሂደት እንደሚተገበር ምሁራን በሥራቸው ገልፀዋል፡፡

## 2.12 የማዳመጥ ችሎታን የመገምገም ሂደት

ግምገማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚካተቱ ሂደቶች አሉ፡፡ የ Mstrevy እና የሥራ ባልደረቦቹ ፈተናዎችን በመንደፍ ላይ ለተካተቱ ሂደቶች የትንታኔ ግልፅነት ይሰጣል፡፡ እንዳየነው ግምገማ በማዕከላዊ ተመልካች እስከ ተፈታኞች እስከምንሰጠው የይገባኛል ጥያቄ ድረስ ያለው አመክኒዮ ሰንሰለት ነው፡፡ በዚህ ላይ የሚወሰኑት ውሳኔዎች ናቸው፡፡ Mestvy ይህንን "የግምገማ ክርክር" ይለዋል፡፡ ይህ የግምገማ መረጃን አስፈላጊነትና ዋጋውን እንደማስረጃ ለማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንደ Mstrevy ገለጻ ተማሪዎች የሚያውቁትን ሊያደርጉ ስለሚችሉት ወይም ስላከናወኗቸው ነገሮች በጣት የሚቆጠሩ ነገሮችን

በሚናገሯቸው፣ በሚያደርጉት ወይም በተለያዩ ቅንጅቶች ላይ በመመስረት ነዉ Mtervy, Steinberg & Almond : (2003, p4)::

## 2.13 የማዳመጥ ግምገማ ዓይነቶች

ንባብን ለመገምገም እና ለመፈተሽ የተለያዩ ዓይነቶች እንዳሉ ሁሉ የማዳመጥ ችሎታን የመገምገምና የመሞከር ዓይነቶችን መለየት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን የማዳመጥ ፍጥነት ለመቆጣጠር ብዙ ጊዜ ባይቻልም ለተለያዩ ግብዓቶች የሚሰጠውን የትኩረት ደረጃ መቀየር ይቻላል፡፡ ሰዎች ለቁምነገር ያዳመጡ ለተወሰኑ ደረጃዎች እየመረጡ ያዳመጡ ወይም በጥልቀት ያዳመጡ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ ይከታተላሉ፡፡ ለመገምገምና በተሳካ ሁኔታ ለመፈተሽ የሚያጋጥሟቸውን የግብዓት ዓይነቶችና ከታሰቡት ዓላማዎች ጋር የሚስማማውን የማዳመጥና የመፈተሽ ዓይነት መምረጥ ጥሩ ነው፡፡

Fild (2008) :: አብዛኞቹ ግምገማዎች እና የማዳመጥ ፈተናዎች በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ በጣም ጠባብ የሆኑትን የነዚህን የማዳመጥ ዓይነቶች ብቻ እንደሚያካትት ተናግሯል፡፡ ብዙውን ጊዜ የማዳመጥ ዓላማ እሱ የማዳመጥ ቅኝት ብሎ በጠራው ወይም ለተወሰኑ ዝርዝሮች ማዳመጥ ብቻ ነው፡፡ ክልሉ በኢላማው የቋንቋ አጠቃቀም ላይ የሚገኘውን ክልል የበለጠ በማንፀባረቅ መስፋፋት እንዳለበት ተከራክረዋል፡፡ አብዛኛው አድማጭ ሰዎች የውጭ ግምገማዎችን የሚያካትቱ ከሌሎች ሰዎች ጋር ፊት ለፊት በሚደረግ ግንኙነት መሳተፍ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ አጫጭር ንግግሮችን ማዳመጥና ለሚሰሙት ነገር ፈጣን ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡ ማዳመጥ አንድ አካል በብዙ የንግግር ግምገማዎች ውስጥ ይሳተፋል፤ ነገር ግን በውጤት መስፈርቱ ላይ ሊያንፀባርቅ ይችላል፡፡

Blackwell A. & Naber T. (2006)፡፡ ጥቃቅን የማዳመጥ ችሎታን፣ ጥቃቅንና የተራዘመ ንግግርን የቋንቋ ስልታዊ መስተጋብርና ውስብስብ ችሎታዎችን ተመልከተዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ተዛማጅ ታክሶኖሚዎች ለተማሪዎች የማዳመጥ ችሎታ ትክክለኛ እና አስተማማኝ ግምገማ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በትክክል መገምገም የምንፈልገውን በትክክል ለይተን ማወቅ በቻልን መጠን ድምዳሜዎቻችንን ይበልጥ በአስተማማኝ ሁኔታ እንወስዳለን፡፡

## 2.14 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማጥናት ስትነሳ ባደረገችው ተመሳሳይነት ያላቸው ርዕሶች አሰሳ ከዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር ቀረቤታ ወይም አንድነት ሊኖራቸው ይችላል ተብለው ከተገመቱት ሥራዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

1. አልማዝ (2006) አላማው በ9ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች እና ክንውኖች የክፍሉ ውስጥ አተገባበርን ሲሆን ውጤቱ የማዳመጥ ክህሎት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንደማይተገበሩት ይገልጻል፡፡
2. ነገሰ (1994) የጥናቱ አላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች የክፍል ውስጥ የማዳመጥ አተገባበር ተገቢነት መፈተሽ ላይ ሲሆን ውጤቱ የተመረጡ መልመጃዎች እና ይዘቶች ለክህሎቱ መጎልበት ከሚረዱ ንድፈ ሃሳቦች አንፃር አለመቅረባቸውን የሚጠቁም እና የክፍል ውስጥ አተገባበር ደካማ እና ጠንካራ ጐኖች አላሳዩም፡፡
3. እቴነሽ (1986) ዋና ዓላማዉ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ላይ የማዳመጥን ክህሎት ማዳበር ሲሆን ፤ይህም ‹‹የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ያዳብራሉ ወይ›› የሚል ሲሆን ዉጤቱም የማዳመጥ ክህሎት በመርሃ ትምህርቱ ዉስጥ ይዘቶቹ ግልጽ ባልሆኑና አሻሚ በሆነ መንገድ ስለተጻፈ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተንተርሶ ለሚያስተምር የቋንቋ መምህራን በየትኛዉ ክህሎት ላይ ማትኮር እንደሚገባዉ በትክክል እንደማያመለክትና የማዳመጥ ክህሎት ከሌሎች ክሂሎች ይዘቶች ብዛት ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጥቂት መሆናቸዉንና የማዳመጥ ክህሎት በቂ ትኩረት እንዳላገኘ ተገልጻል፡፡
4. ጥላሁን (2003) የጥናቱ ዋና አላማ የመዳመጥ ክህሎትን ከንግግር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚተገበር አቀራረብ ላይ ያተኮረ ጥናት ሲሆን የዚህ ጥናት ዉጤት መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸዉ ግንዛቤ ጥሩ እንደሆነ ቢገልጹም መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ትኩረት ሰጥተዉ በቅንጅት እንደማያቀርቧቸዉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከፍ ብለዉ የተዳሰሱት ጥናቶች የሚያነሳቸዉ ርዕሰ ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል ወይም በሙሉ የሚመሳሰሉም ቢሆኑም እንደዚሁ ልዩነታቸዉም የጎላ ነዉ፡፡ ይኸዉም፤ የአልማዝ አለማየሁ እና የእቴነሽ ተገኘን ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ በማዳመጥ ክህሎት ይዘቶች የክፍል ዉስጥ አተገባበር ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከሁለቱ ጥናት የሚለይበት ነጥቦች ጥናቱ የሚጠናዉ በኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ የሚጠና መሆኑ፤ በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መርሃ ትምህርት ላይ የሚጠና መሆኑና በ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ማለትም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ማዕከል (ትኩረት) ያደረገ ጥናት ነዉ፡፡

የጥላሁን ከበደ እና የነገሰ ገ/ጻዲቅ ጥናቶች ከዚህ ጥናት የሚለየዉ ፤ የጥላሁን ጥናት የማዳመጥ ክህሎትን ከንግግር ክህሎት ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ላይ ያተኩራል፡፡ የነገሰ ገ/ጻዲቅ ጥናት ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዉስጥ የማዳመጥ ክህሎትን ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች፤ መልመጃዎች የክፍል ዉስጥ ግምገማ ላይ የሚያተኩር ጥናት ነዉ፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነቱ የጎላ ነዉ፡፡ እንደዚሁ በኢንግሊእኛ የተጠናዉ ነብሩ (2020) ዋናዉ ትኩረቱ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት መሠረታዊ ግምገማ ላይ ያተኮረ ጥናት ነዉ፡፡

በመሆኑም ይህንን ጥናት ከሁሉም ጥናቶች ልዩ የሚያደርገዉ ነጥብ ፤ አራቱም ጥናቶች የተጠኑት የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ትኩረት ያደረገ ጥናት ነዉ፤ አራቱም ጥናት በአፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ የተጠና ጥናት ነዉ፡፡ ይህ ጥናት ግን የሚጠናዉ ከአራቱም የሚጠናበት ቦታ፣ የሚማሩበት የክፍል ደረጃ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልዩነት የተጠናበት ጊዜና ሁኔታ የሚያደርጉት ነጥቦች ከዚህ በታች ቀርቧል፡ -

1. በአዲሱ ፍኖተ ካርታ የተዘጋጀ መርሃ ትምህርት ላይ የተደረገ ጥናት ነዉ፡፡
2. በኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች ላይ የሚጠና ጥናት ነዉ፡፡
3. በ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ የሚጠና ጥናት ሲሆን በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት አራቱ ጥናቶች ጋር ሲነጻጸር በቦታ፣ በጊዜ፣ በክፍል ደረጃ፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ልዩነትና በመማሪያ መፅሐፍ ይለያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት የሚከተለዉ የአጠናን ዘዴ ዐይነታዊ የምርምር ዘዴ ክፍል የሆነዉን ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፤ በቀጣይነትም ተጠኚዎች ላይ የሚታይ የባህሪይ ለዉጥ መምጣቱንና አለመምጣቱን ለማወቅ ያስችል ዘንድ የማዳመጥ ክሂል ደረጃዎችን ለምሳሌ የቅድመ ማዳመጥ፣ የማዳመጥ ጊዜ እና የድህረ ማዳመጥ ጊዜ ክንዉንና ትግበራ ተጠኚዎችን በማለማመድ፡፡ ተጠኚዎቹም ከክንዉኑ በፊት፣በክንውን ጊዜና ከክንውኑ በኋላ የሚያመጡትን የባህሪይ ለዉጥ ለመለየት የጽሑፍ መጠይቆችንና ቃለ መጠይቆችን በመሙላት ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ዐይነት

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አማካይነት የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለጥናቱ ዐይነት አመቺ የሆነ የክፍል ውስጥ ምልከታን ለመጠናዊ የአጠናን ስልት፣ የጽሑፍ መጠይቅና ዳግም ለአይነታዊ የአጠናን ስልት የተጠቀመ ሲሆን የጥናቱም አይነት መጠናዊ እና አይነታዊ የጥናት ዓይነት ነው፡፡

### 3.2 የናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ክንውኖች አተገባበር በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ ትምህርት ቤት ነው፡፡

#### 3.2.2 የመምህራን አመራረጥ

በአርሲ ዞን ደዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ 1ኛና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ከሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አምስት መምህራን ጠቅላይ የናሙና ዘዴን በመጠቀም አምስቱም መምህራን ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ 1ኛ ና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በመማር ላይ የሚገኙት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎተ የ8ኛ ሀ፣ 8ኛ ለ እና 8ኛ ሐ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ50-55 ተማሪዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል ወካይ የሚሆኑ ተማሪዎችን በተራ የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ አማካይነት 50%(75) የሚሆኑ ተማሪዎች በጥናቱ ዉስጥ ተካተዋል።

## 3.3 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የሚካተቱት ትምርት ቤት፤ የክፍል ደረጃ፤ የመምህራንና ተማሪዎች መረጣ ከተከናወነ በኋላ መረጃዎችን በተለያዩ ዘዴዎች አማካይነት መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተካሂዷል። ይህንን ለማድረግ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለዉ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ሲሆን በአጋዥነት የመምህራን ቃለ መጠይቅና የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ በመዋል መረጃዎች ተሰብስባል። የቃል መጠይቁ ለመምህራን የቀረበበት ምክንያት የመምህራን ቁጥር አምስት በመሆኑ አስፈላጊዉን መረጃ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ስለታሰበ ነዉ።

### 3.3.1 ምልከታ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ ምልከታ የመረጃ ማግኛ መንገዶች ሁለት ናቸው። እነሱም ተሳታፊ እና ኢ-ተሳታፊ ይባላሉ። በተሳታፊነት የሚደረግ ምልከታ እጥኚው በክፍል ውስጥ ተግባር ተሳታፊ በመሆን የሚያከናውነው ሲሆን በኢ-ተሳታፊነት የሚደረግ ምልከታ ደግሞ አጥኚው በድርጊቱ ተሳታፊ ሳይሆን መረጃ ለመሰብሰብ ብቻ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ የሚካሄደው የምልከታ ሂደት ነው። ለዚህ ጥናት በዋናነት ተግባራዊ የሆነውም ኢ-ተሳታፊነት የመከታተያ ቅፅና በተሳታፊነት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች መተግበር ያለመተግበሩን በተዘጋጀው የመከታተያ ቅፅ አማካይነት በማየት ነው።

### 3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በጥናቱ ተተኳሪ በሆነ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙት የ8ኛ ክፍል መምህሪንና ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበርን አስመልክቶ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ጥናቶች የተጠቀሙበተን መጠይቅ እንደ ሞዴል ተወስዶ ከጥናቱ ጋር እንዲስማማ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

### 3.3.3 ቃለ መጠይቅ

ከጽሑፍ መጠይቅና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ የጥናቱ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ቃለ መጠይቁ በጥናት ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ ለሚገኙት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን አላማዉም መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የማዳመጥ ክሂልን እንዴት እያቀረቡ እንደሆነ፤ ስለማዳመጥ አቀራረብ ያላቸዉን ግንዛቤና የማዳመጥን ክሂል ሲተገብሩ ስለገጠማቸዉ ችግር መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነዉ፡፡

### 3.3.4 የሰነድ ፍተሻ

የማዳመጥ ክሂል የይዘቶችንና ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበርን ለመገምገም የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በዚህ ጥናት ውስጥ የዋለው ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ ፍተሻ የተደረገው በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መርሐ ትምህርት ወይም መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ይዘቶችን መፈተሽና ይዘቶቹ ለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች አተገባበር ብቁ ናቸውን? የሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን አጥኚዋ በጥናቱ ውስጥ ፍተሻን ተጠቅማለች፡፡

ይህንኑ ተግባር ለማጠናከር ቦርግ እና ጋል (1989 ) ከይዘት ትንተና ጥናት አላማዎች አንዱ የሚጠናዉ ጉዳይ ገላጭ ትንተናን ወይም መረጃን መስጠት መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ስለዚህ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆነዉን በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መርሃ ትምህርት ዉስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበርን፣ የመረጃ ምንጮች አመራረጥን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና አደረጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሒደትን መሰረት በማድረግ የአጠናን ስልቱንም አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመከተል

አሃዛዊ የአጠናን ስልትን ደግሞ በደጋፊነት በመጠቀም አቀራረቡ ደግሞ ገለጻዊ (descriptive method) የአተናተን ዘዴን የተከተለ ጥናት ነዉ፡፡

### 3.3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ ትንታኔ ያገለገሉ መረጃዎች በሶስት መረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ አንደኛ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ የተከናወኑ ክንውኖች የምልከታ ማስታወሻ ተሰብስቧል፡፡ ይኸውም የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ፣ ቃለመጠይቅ ለተጠኚዎች በማዘጋጀት፣ የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀት ተማሪዎችን በመጠየቅ ከላይ በተዘረዘሩት መረጃ መሳርያዎች በመቅረፀ ድምፅ የተዘጋጀ፣ በስእል፣ በካርታ እና በሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁ መሳርያዎችን መጠቀም፤ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የማዳመጥ ክህሎትን ማለማመድ ውጤታማነቱ የጎላ መሆኑን Anderson & Lynch (1991፣18) ይህን ሀሳብ በመደገፍ ማዳመጥን ማስተማር ጥሩ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

በዚህ መልኩ የተሰበሰበ መረጃ ተገቢነቱ ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ርእሰ ጉዳይ ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት ያስችላሉ፡፡ የሚነገርበትንም አውድ ለመለየት ያስችላል፣ ሀሳቦችን በየፈርጁ ለማደራጀት፣ መረጃን ለመለየት፣ ለመፈለግ እና ለማግኘት እንዲሁም ዝርዝር መረጃን ለመረዳት ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ መረጃና ግንዛቤን ለማግኘትና የማዳመጥ ችሎታን ለመገምገም ያስችላል፡፡

## 3.4. የመረጃ አተናተን

በጥናቱ ከምልከታ እንዲሁም ከፅሁፍ መጠይቆቹ የተገኙ መረጃዎችን በማጠናቀር በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎችን የማዳመጥ ክሂል ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበርን በዝርዝር የሚያመለክቱ በመሆናቸው ትንተናው አይነታዊ ዘዴን በመጠቀም በክፍል ምልከታው እንዲሁም የፅሁፍ መጠይቆች ውጤቶችን በአይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አሃዛዊ የምርምር ዘዴን በደጋፊነት ሲጠቀም አቀራረቡ ገለፃዊ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# 4. የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መርሀ ትምህርት ዉስጥ የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግምገማ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን የዚህ ጥናት አጠናን ስልትም አ የምርምር ዘዴን በዋናነት የሚጠቀም ፣አሃዛዊ ዘዴን ደግሞ እንደ አስፈላጊነቱ በደጋፊነት የሚጠቀም ሲሆን አቀራረቡም ገለጻዊ ወይም ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ መሆኑን በምዕራፍ ሦስት ዉስጥ ከግብ እንደሚደርስ ተጠቅሷል፡፡ የመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት የተማሪዎች ፅሑሁፍ መጠይቅ የክፍል ዉስጥ ምልከታ እና የመምህራን የቃለ መጠይቅ መሆኑን ከላይ በተጠቀሰዉ ምዕራፍ ዉስጥ ተጠቁሟል፡፡ በዚህም መሠረት አጥኚዋ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ በመቀጠልም በእያንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች (መጠይቆች) በዓላማቸዉ መሠረት ከዚህ በታች እንደሚከተለዉ በሰንጠረዥ ዉስጥ ተተንትኗል፡፡

### ሰንጠረዥ 4.1፡ የተጠኚ መምህራንና የትምህርት ቤት አደረጃጀት መግለጫን የሚያሳይ

| ተ.ቁ | ት/ቤት | መምህር | የመምህራን ዳራዊ መግለጫ | | | የተመረቀበት የት/ት ዓይነት | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጾታ | እድሜ | የት/ት ደረጃ | | |
| 1 | አርጊቲ ደነባ | መ/ርት1 | ሴ | 28 | ድግሪ | አማርኛ | 15 |
| | | መ/ር2 | ወ | 42 | ድግሪ | አማርኛ | 30 |
| | | መ/ርት3 | ሴ | 30 | ድግሪ | አማርኛ | 12 |
| | | መ/ር 4 | ወ | 43 | ድግሪ | አማርኛ | 32 |
| | | መ/ር 5 | ወ | 32 | ድግሪ | አማርኛ | 33 |

በሰንጠረዡ ዉስጥ የተገለጸዉ በናሙናነት የተመረጠ ትምህርት ቤት ስም አርጊቲ ደነባ 1ኛ ደረጃ ሲሆን ሰንጠረዡ የሚያስረዳዉ አምስቱ ተጠኚ መምህራን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጥናቱ አካል የሆኑ ናቸዉ፡፡ እነዚህ የተገለጹት፣ ከአምስቶቹ መምህራን ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ፣ ሦስቱ ደግሞ ወንዶች መሆናቸዉን ያሳያል፡፡ በተጨማሪም በሰንጠረዡ ዉስጥ በእድሜ፣ በትምህርት ዝግጅታቸዉ፣ በተመረቁበት የትምህርት ዓይነትና የሥራ ላይ ቆይታ የአገልግሎት ዘመንም የተገለጸበት መሆኑን ያስረዳል፡፡

## ሰንጠረዥ4.2፡- የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ (ሁኔታ) ን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ፡-

| ተ.ቁ | ጾታ | | እድሜ | | የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሁኔታ | | ከክፍል ውጪ የሚጠቀሙበት ቋንቋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ከ13-18 | ከ18 በላይ | ኦሮሚኛ | አማርኛ | ኦሮሚኛ | አማርኛ |
| 1 | 46 61% | 29 38.6% | 55 73% | 20 26% | 65 86.6% | 10 13.3% | 65 86.6% | 10 13.3% |
| ድምር | 75 | | 75 | | 75 | | 75 | |

የሰንጠረዡ መግለጫ የሚጠቁመዉ የተጠኚ ተማሪዎችን የጾታ ሁኔታ፣ የእድሜቸዉን ሁኔታ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልዩነት እና አብዛኛዉን ጊዜ ከክፍል ዉጪ የሚጠቀሙበት ቋንቋቸዉን የሚገልጽ ነዉ፡፡

በዚህ መሠረት የተጠኚዎቹን ከፍተኛ ቁጥር የያዘዉ ጾታ የወንዶች ጾታ ሲሆን የሴቶች ቁጥር ደግሞ አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ የእድሜያቸዉም ሁኔታ ሲታይ ከፍተኛዉን ቁጥር/ ብዛት/ የሚያሳየዉ ከ13-18 የእድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ትልቁን ቁጥር መያዛቸዉን ያሳያል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልዩነት ሲታይ በጣም ከፍተኛ ቁጥር የያዘዉ የኦሮሚኛ ቋንቋ አፍ ፈት መሆናቸዉን ያሳያል፡፡ ከዚህ ዉስጥ የአማርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ወይም ሁለቱንም ቋንቋ የሚጠቀሙ የተጠኚዎች ቁጥር በጣም ጥቂት መሆናቸዉን ያሳያል፡፡ እንዲሁም ከክፍል ዉጪ አብዛኛዉን ጊዜ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ኦሮሚኛ ቋንቋ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ይህ ደግሞ የማዳመጥ ክሂላቸዉን በተፈለገዉ ደረጃ ለማሻሻል እንዲችሉ ተግዳሮት እንደሆነባቸዉ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡ ምክንያቱም አማርኛ ቋንቋን የሚማሩት እንደነሁለተኛ ቋንቋ ስለሆነ ተጠኚዎቹ በማዳመጥ ክሂል ክፍለ ጊዜ ሁል ጊዜ የትምህርቱ ቋንቋ እንዲተረጎምላቸዉ የሚጠይቁ መሆናቸዉን አጠኚዋ ተገንዝባለች፡፡

ይህ ደግሞ የታላሚዉን ቋንቋ የማዳመጥ ችሎታቸዉን የሚያቀጭጭ መሆኑን አጥኚዋ ታምናለች፡፡ ምክንቱም ክሂሉን የሚማሩት በሁለተኛ ቋንቋቸዉ ስለሆነ ተጠኚዎቹ በማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ፍላጎት የማጣት ስሜት ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተጠኚዎቹ ለክሂሉ ፍላጎት እንዲኖራቸዉ የመምህራን ሙያዊ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸዉም አጥኚዋ ታምናለች፡፡

ይህንኑ ለማጠናከር ጆናታን ማርክ እና ሉዛንግ (2016) ማዳመጥን ለማስተማር አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች ፡-የተቀረጹ ድምጾችን መጠቀም፣ ትእይንቶችን ማሳየት፣ ገጸባህሪያትን ማስተዋወቅ፣ መዝገበ ቃላትንና የመሳሰሉትን በመጠቀም የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ለማስተማር ተማሪዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ በቀዳሚዉ ምራፍ ሁለት ገጽ12 ላይ ተጠቅሷል፡፡

## 4.2 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር

ቀደም ሲል ምዕራፍ ሁለት (2.4.1) በክለሳ ድርሳን ዉስጥ በቅድመ ማዳመጥ ክንዉን ደረጃ ምሁራን ሲገልጹ በዚህ ደረጃ መምህራን በክፍል ዉስጥ የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ፣ ከትምህርቱ ርዕስ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እዉቀታቸዉን መመዘን፣ ተማሪዎቹ በትምህርቱ ዙሪያ ይነገራል ብለዉ የሚጠብቁትን ሀሳብ ወይም ቁም ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ እንደሚገባ Anderwood (1989) በክለሳ ድርሳን ዉስጥ ገልጸዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 4. 3፡የክፍለ ጊዜዉ የቅድመ ማዳመጥ ክህሎት ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ምልከታ የተገኘ ምላሽ**

| ተ፣ቁ | የመከታተያ የፅሑፍ መጠይቆች | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አልፎ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | **የቅድመ ማዳመጥ ጊዜ** | | | | | | |
| 1.1 | በቅድመ ማዳመጥ ክሂል ክንዉን ወቅት ይዘቱን በሰሌዳ ላይ ፅፈዉ ያስተዋዉቃሉ? | 15 | 23% | 5 | 7% | 45 | 69% |
| 1.2 | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረበዉ የቅድመ ማዳመጥ ክሂል ትምህርት ጥያቄዎች ግልጽነትና ብቃት አላቸዉ? | 12 | 18% | 13 | 20% | 35 | 53.8% |
| 1.3 | መምህሩ ርዕሱን ካስተዋወቁ በኋላ ስለ ርዕሱ ምን ምን ፍሬ ሃሳብ ሊነሱ እንደሚችሉ እንድትገምቱ ያደርጋሉ? | 10 | 15% | 20 | 30.7% | 35 | 53,8% |
| 1.4 | የመማሪያ ክፍል ሥነ ሥርዓት ለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውን ምቹነት አለዉ? | 25 | 38% | - | - | 40 | 61.5% |

በዚህ ጥናት የተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የክፍል ዉስጥ ምልከታ በሚካሄድበት ወቅት መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡት ተጠኚ ተማሪዎች ብዛት ወንድ 46 ሴት 29 ድምር 75 ተጠኚዎች መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በምልከታዉ ጊዜ መጠይቁን የሞሉት ወንድ 42 ሴት 23 በድምሩ 65 ተጠኚዎች መጠይቁን ሲሞሉት አስር(10) ተጠኚዎች መጠይቁን ሳይሞሉት ቀርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት ከታች በቀረበዉ ሰንጠረዥ ምላሽና ትንታ ዉስጥ የተገለጹት የተጠኚዎች ብዛት 65 መሆኑን ያሳያል፡፡

በሰንጠረዥ ሦስት ላይ በቅድመ ማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንዉን ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

**ጥያቄ** 1.1.:- በቅድመ ማዳመጥ ክህሎት አተገበበር ጊዜ መምህራችሁ ይዘቱን በሰሌደ ላይ ጽፈዉ ያስተዋዉቃሉ? ለሚለዉ ጥያቄ ለተጠኚዎች ቀርቦ፤ 15(23%) አዎን፣ 5(7%) አይደለም፣ 45(69%)አልፎ አልፎ ይጽፋሉ በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ ምላሽ የሚያሳየዉ ይዘቱ አልፎ አልፎ በሰሌዳዉ ላይ እንደሚፃፍ ያስረዳል፡፡

**ጥያቄ** 1.2 ፡-በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡ የቅድመ ማዳመጥ ክሂል ትምህርት ጥያቄዎች ግልጽነትን በተመለከተ 12(15%) አዎን፣ 38(50%) አይደለም፣15(23%) ደግሞ አልፎ አልፎ ግልጽ ነዉ በማለት መልሰዋል፡፡የተማሪዎቹ ምላሽ የሚጠቁመዉ የቀረቡት ጥያቄዎች ግልጽነት አልፎ አልፎ እንደሆነ የተማሪዎቹ ምላሽ ያሳያል፡፡

**ጥያቄ** 1.3፡-መምህሩ ርዕሱን ካስተዋወቁ በኋላ ርዕሱን በተመለከተ ምን ምን ፍሬነገር ሊነሱ እንደሚችል መገመትን በሚመለከት የተሰጠ የተማሪዎች መልስ 10 (15%) አዎን፣ 20(30.7%) አይደለም፣ 35 (53.8%)ደ ግሞ አልፎ አልፎ እንደሚገምቱ ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ**1.4፡- ለቅድመ ማዳመጥ ክህሎት ክንዉን የመማሪያ ክፍል ሥነ-ስርዓት ለማዳመጥ ትምህርት ክንዉን ምቹነት አለዉ? ለሚለዉ ጥያቄ 25(38%) አዎን፣ 40 (61.5%) ደግሞ አልፎ አልፎ መሆኑን መልሰዋል፡፡ ይህ ምላሽ የሚያሳየዉ ክንውኑ አልፎ አልፎ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በጥቅሉ ከላይ በቀረበዉ ትንተና ላይ ከተገኘዉ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለዉ በመጠይቁ የቀረበዉን ክንዉን በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ አብዛኛዉን ጊዜ አልፎ አልፎ የሚተገበር መሆኑን ነዉ፡፡

## ሰንጠረዥ 4.4፡ የክፍለ ጊዜዉ የቅድመ ማዳመጥ አተገባበር ከመምህራን የቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

| ተ.ቁ | የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አልፎ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | የቅድመ ማዳመጥ ጊዜ | | | | | | |
| 1.1 | የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በክፍል ዉስጥ ለተማሪዎች መቅረቡ አስፈላጊ ነዉ ብለዉ ያምናሉ? | 4 | 80% | - | - | 1 | 20 % |
| 1.2 | በቅድመ ማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ርዕሱን በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ለተማሪዎች ያስተዋዉቃሉ? | 3 | 60% | - | , | 2 | 40 % |
| 1.3. | በቅድመ ማዳመጥ ክፍለ ጊዜ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ? | 2 | 40% | -- | - | 3 | 60 % |
| 1.4. | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ብቁናቸዉ? | 3 | 60 % | | | 2 | 40 % |

ሰንጠረዥ አራት፡- የቅድመ ማዳመጥ አተገባበር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ትንተና ዉስጥ **ጥያቄ** 1.1. የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት በክፍል ዉስጥ መተግበሩ አስፈላጊ ነዉ ብለዉ ያምናሉ? ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠዉ ምላሽ 4 (80%) አዎን፣ 1(20%) ደግሞ አልፎ አልፎ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ** 1.2፡- በቅድመ ማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ርዕሱን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ለተማሪዎች ያስተዋዉቃሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 3(60%) አዎን፣ 2(40%) አልፎ አልፎ ርዕሱን በመፃፍ እንደሚያስተዋዉቁ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ** 1.3. በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 2(40%) አዎን፣ 3(60%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩ መልሰዋል፡፡

**ጥያቄ** 1.4. በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ግልጽ ናቸዉ? ለሚለዉ መጠይቅ 3(60%) አዎን፣ 2(40%) አልፎ አልፎ ግልጥ ነዉ በማለት መልሰዋል።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበዉ ትንተና የተገኘዉ  ምላሽ  ሁሉም ተጠኚዎች አብዛኛዎቹን መጠይቆች አልፎ አልፎ በማለት እንደሚተገብሩ ምላሽ ሰጥተዋል።

ቀጥሎ በሰንጥረዥ ሦስት የተጠኚ ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅና ሰንጠረዥ አራት የተጠኚ መምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘዉ ምላሽ ምን እንደሚመሥል ከዚህ በታች ቀርቧል። በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ሰንጠረዥ ሦስት

ጥያቄ 1.1. መምህራችሁ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ ይዘቱን ወይም ርዕሱን ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያስተዋዉቃሉ? ለሚለዉ መጠይቅ የተጠኚዎቹ ምላሽ 15 (23%) አዎን፣ 5 (7%) አይደለም፣ 45 (65%) አልፎ አልፎ የተገብራሉ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ ሰንጠረዥ አራት ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ጥያቄ 1.2. የተገኘዉ ምላሽ 4(80%) አዎን ፣ 1(20%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩ ምላሽ ሰጥተዋል።

በዚህ አተገባበር ሂደት ከተጠኚዎች የተሰጠዉ ምላሽ ልዩነት አለዉ ። ይሔዉም ተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ 45 (65%) አልፎ አልፎ የሚተገበር መሆኑን ሲገልጹ፤ የተጠኚ መምህራን ምላሽ ግን (80%) አዎን የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለዉ አራቱ መምህራን ይዘቱን አዎን በማለት እንደሚተገብሩ ሲገልጹ አንዱ መምህር አልፎ አልፎ እንደሚተገብር ገልጸዋል። የተማሪዎችን ምላሽ ስንመለከት ደግሞ 45 (65%) እንደማይተገበር ገልጸዋል። ስለዚህ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለዉ ይዘቱ እንደሚተገበር ያሳያል።

ከላይ በተጠቀሰዉ ሰንጠረዥ የተጠኚ ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ጥያቄ 1.2. በአዲሱ ፍኖተ ካርታ የተማሪ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቅቡ የቅድመ ማዳመጥ ክሂል ትምህርት ጥያቄዎች ግልጽነትና ብቃት አላቸዉ? ለሚለዉ መጠይቅ እና የተጠኚ መምህራን ቃለ መጠይቅ ጥያቄ 1.4. ተመሳሳይ መጠይቅ ላይ የተገኘዉ ምላሽ ልዩነት አለዉ። ለምሳሌ ጥያቄ 1.2. ላይ የተሰጠዉ ምላሽ 10 (15%) አዎን፣ 35 (53.8%) አይደለም፣ 20 (30.7%) አልፎ አልፎ ይተገበራል የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን፤ ጥያቄ 1.4. የመምህራን ቃለመጠይቅ ላይ

የተሰጠዉ ምላሽ 3 (60%) አዎን፣ 2 (40%) አልፎ አልፎ የተገበራል የሚል ምላሽ ሰጠተዋል፡፡ እዚህ ላይ ተጠኚ ተማሪዎች 53.8% አይደለም ሲሉ ተጠኚ መምህራን 60% ደግሞ አዎን ብለዉ መልሰዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ብቃት እንዳላቸዉ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.3 የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት የድህረ ማዳመጥ አተገባበር

ለዚህ ጥናት ንድፈ ሃሳበዊ ቅኝት ሲካሄድ በክለሳ ድርሳን 2.4.2. ገጽ16 ላይ የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ላይ ተማሪዎች የሚደመጠዉን ርዕሰ ነገር በጥልቀት የሚያዳምጡበትና ተፈላጊ መረጃዎችን የሚሰበስቡበት ነዉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚደመጠዉን ፅሑፍ ወይም ንግግር በተመስጦ በመከታተል እና ማስታወሻ በመያዝ ልምምዱን በተገቢዉ ሁኔታ እንዲያካሄዱ የሚደረግበት ደረጃ ነዉ፡፡ በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን ተማሪዎች ስዕሎችን በትክክለኛዉ ቅደም ተከተላቸዉ እንዲያስቀምጡ፣ ያልተሟሉ መረጃዎችንና እቅዶችን እንዲያሟሉ፣ አንድን ፅሑፍ ወይም ንግግር እያዳመጡ ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንደሚችል እነዲገምቱ፣ የሚነገረዉን ነገር በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸዉ ላይ እንዲያሰፍሩ፣ አያያዥ ቃላትን የተለየ ትኩረት ሰጥተዉ እንዲያዳምጡ ማድረግ ይገባቸዋል በማለት ገልጸዋል (በድሉ፣1996)::

## ሰንጠረዥ 4.5፡የክፍለ ጊዜዉ የማዳመጥ ጊዜ ክሂል አተገባበር ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተደረገዉ ምልከታ የተገኘ ምላሽ

| ተ.ቁ. | የፅሑፍ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አ፤ፎ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 2 | የማዳጥ ጊዜ | | | | | | |
| 2.1. | መምህራችሁ እያንዳንዱን አንቀጽ በእርጋታ ያነቡላችኂ? | 9 | 13% | 21 | 32% | 35 | 55% |
| 2.2. | መምህራችሁ ንግግር ወይም ምንባብ በሚያነቡላችሁ ጊዜ በመሀል ቆም እያሉ በቀጣይ ምን ሊሆን እንደሚችል እንድትገምቱ ያደርጋሉ? | 18 | 27.8% | 12 | 18.4% | 35 | 53.8% |
| 2.3. | የተለያዩ ታሪኮችንና የተቀረጹ ድምጾችን ወደ ክፍል በማምጣት እንድታዳምጡ ያነቡላችኂል? | 10 | 15.5% | 35 | 53.8% | 20 | 30.7% |
| 2.4. | በማዳመጥ ጊዜ የንግግሩን ወይም የምንባቡን መልእክት እንድትረዱ በቂ ጊዜ ሰጥተዉ ጽሁፉን በድጋሜ ያነቡላችኂል? | 15 | 23.8% | 38 | 48.4% | 11 | 17.8% |

በሰንጠረዥ 4.5 በማደመጥ ጊዜ ክንዉን ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ፡- ጥያቄ 2.1. መምህራችሁ እያንዳንዱን አንቀጽ በእርጋታ ያነቡላችኂል? ለሚለዉ መጠይቅ 9(13%) አዎን፣ 21(32%) አይደለም፣ 35(53%) አልፎ አልፎ ያነባሉ በማለት መልሰዋል፡፡

ጥያቄ 2.2.መምህራችሁ ንግግር ወይም ምንባብ በሚያነቡላችሁ ጊዜ ማራኪነት አለዉ? ለሚለዉ መጠይቅ 18(27%) አዎን፣ 12(18%) አይደለም፣ 35(53.8%) አልፎ አልፎ ማራኪ ነዉ በማለት መለሰዋል፡፡

ጥያቄ 23.መምህራችሁ የተለያዩ ታሪኮችን ወደ ክፍል በማምጣት እንድታዳምጡ ያነቡላችኂል? ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠዉ ምላሽ 22.(33.8%)አዎን፣ 38(58%)አይደለም፣ 25(38%) አልፎ አልፎ ያነቡልናል በማለት መልሰዋል፡፡

ጥያቄ 2.4.በማዳመጥ ጊዜ የንግግሩን ወይም የምንባቡን መልእክት እንድትረዱ በቂ ጊዜሰጥተዉ ፅሑፉን በድጋሚ ያነቡላችኂል? ለሚለዉ መጠይቅ 22(33.8%) አዎን፣ 38(58.4%) አይደለም፣ 25(38%) አልፎ አልፎ ያነቡልናል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በዚህ ትንታኔ ምላሽ ላይ የሚታየዉ ግብረ መልስ ትግበራዉ አልፎ አልፎ የሚተገበርና አንዳንዴም የማይተገበር መሆኑን ያሳያል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.6፡ የክፍለ ጊዜዉ የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና

| ተ.ቁ | የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች | አ ማ ራ ጮ ች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አልፎ | |
| | | በቁጥር | / | በቁጥር | / | በቁጥር | / |
| 2 | የማዳጥ ጊዜ | | | | | | |
| 2.1 | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ጊዜ ክህሎት ምንባብ እያንዳንዱን አንቀጽ ለተጠኚዎቹ በእርጋታ ያነቡላችኂል ? | - | - | 3 | 60% | 2 | 40% |
| 2.2. | በማዳመጥ ጊዜ ምንባብ ወይም ንግግርን እያስደመጡ በመሀል ቆም እያሉ ቀጣዩን ሀሳብ እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | 1 | 20% | 4 | 80% | - | - |
| 2.3. | ለክህሎቱ ማስተማሪያነት የተቀረጹ ድምጾችን ፣ ስእል፣ ካርታና በሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁን የትምህርት መርጃወችን በክፍለ ጊዜዉ ይጠቀማሉ? | - | - | 3 | 60% | 2 | 40% |
| 2.4. | በማዳመጥ ጊዜ የሚደመጠዉን ርዕሰ ጉዳይ ከራሳቸዉ ልምድና ከአካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያመሳክሩ ያደርጋሉ? | 2 | 40% | 3 | 60% | - | - |

**ሰንጠረዥ 4.6፡-** የማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ጥያቄ 2.1. በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መፅሐፍ ዉስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክህሎት ጥያቄዎች ቁልፍ ቃላትን ለማስተማር ብቃት አለዉ? ለሚለዉ መጠይቅ 3(60%) ተጠኚዎች አዎን፣ 2(40%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እተገብራለሁኝ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 2.2. በማዳመጥ ጊዜ ምንባብ ወይም ንግግር እያስደመጡ በመሃል ቆም እያሉ ቀጣዩን ሀሳብ እንዲገምቱ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 1(20%) ተጠኚዎች አዎን ብለዉ ሲመልሱ 4(80%) ተጠኚ ደግሞ አይተገበርም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 2.3. ለክህሎቱ ማስተማሪያነት የተቀረጹ ድምጾችን፣ በስዕል፣ በካርታና በሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁ የክህሎቱን መርጃዎችን በክፍለ ጊዜዉ ይጠቀማሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 3(60%) ተጠኚዎች አልጠቀምም ወይም አይደለም ብለዉ የመለሱ 2(30%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁኝ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 2.4 .በማዳመጥ ጊዜ የሚደመጠዉን ርዕሰ ጉዳይ ከራሳቸዉ ልምድና ካካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያመሳክሩ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 2(40%) ተጠኚዎች አዎን፣ 3(60%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከለይ የቀረበዉ ትንተና የሚያሳየዉ ምላሽ ሦስቱ ተጠኚዎች አዎን ብለዉ ሲመልሱ ሁለቱ ተጠኚ ደግሞ አልፎ አልፎ እተገብራለሁ በማለት እደሚተገብሩ መልሰዋል፡፡

ከላይ የተገለጸዉ ትንተና የሚያስረዳዉ ትግበራዉ በሦስቱም ተጠኚዎች በኩል የማይተገበር መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህንን ምክንያት ተጠኚ መምህራን ሲያስረዱ ተጠኚ ተማሪዎች ፍላጎት የሌላቸዉ መሆኑን፣ ለክፍለ ጊዜዉ የተሰጠ ሰዓት በጣም አጭር መሆኑን፣ ራሳቸዉመምህራን ትኩረት የማይሰጡ መሆናቸዉን ገለጸዋል፡፡

## 4.4. የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ የክፍል ዉስጥ አተገባባር

በክለሳ ድርሰን 2.4.3. ገጽ 16-18 ላይ ለዚህ ጥናት ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ሲካሄድ ድህረ ማዳመጥን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ለዚህ ክፍል ብይን ሰጥተዋል፡፡

Ricson (1986፣72) በድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ንግግር ወይም ጸሁፍ መሰረት በሀሳብ መስማማትና አለመስማማታቸዉን ወይም ያዳመጡትን ከግላዊ ገጠመኝ ጋር በማዋሃድ ሊመልሷቸዉ የሚችሉትን ጥያቄዎች እንደ ተማሪዉ ማንነት በመጠየቅ የማዳመጥ ችሎታን የሚያዳብሩበት ደረጃ ነዉ በማለት ገልጸዋል፡፡

Snow & Pricnis (1979) እንደ ገለጹት ድህረ ማዳመጥ ተማሪዎች የፈለጉትን ወይም የጠበቁትን መረጃ በትክክል ማግኘትታቸዉን ወይም አለማግኘታቸዉን የሚያረጋግጡበት፣ ይዘቱን ወይም ሪዕሱን በጥልቀት ለመመርመርና የተናጋሪዎችን ዝንባሌ ለማወቅ የሚሞክሩበት ደረጃ ነዉ፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ምጋቤ ምላሽ በቃል መስጥት፣ ተማሪዎቹ በጥንድ፣ በቡድንንና በጋራ በመሆን የተሰጡትን መልሶች እንዲያመሳክሩ ማድረግ፣ በንግግሩ ወይም በተደመጠዉ ፅሑፍ ዉስጥ ሊያከራክሩ የሚችሉ ነገሮችን በመምረጥ ተማሪዎቹ እንዲከራከሩ ማድረግ፣ ባዳመጡት ፅሑፍ ዉስጥ የተሰማቸዉን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፣ ወዘተ… በዚህ ደረጃ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባሮች ናቸዉ በማለት ገልጸዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.7፡ የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ ክህሎት ትምህርት አተገባበር ከተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ በተደረገዉ ምልከታ የተገኘ ምላሽ**

| ተ.ቁ. | የመከታተያ የጽሁፍ መጠይቆች | አማራጮች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አልፎ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | **ድህረ ማዳመጥ** | | | | | | |
| 3.1.. | በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተራችሁ ላይ በመፃፍ መልሱን እንድትገልጹ ያደርጋሉ? | 20 | 26% | 15 | 17% | 30 | 57% |
| 3.2. | በድምጽ የተቀረጹ ማስተማሪያዎችን አድምጣችሁ መልእክቱን እንድትገልጹ ያደርጋሉ ? | 7 | 11% | 50 | 66% | 15 | 23% |
| 3.3. | ካዳመጣችሁ በኂላ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተረዳችሁትን አስተያየት እንድትሰጡ ያደርጋሉ ? | 20 | 30% | 13 | 20% | 32 | 50% |
| 3.4. | ስነ ጽሁፋዊ ስራዎችን ወደ ክፍል በማምጣት መልእክታቸዉን እንድት ገልጹ ያደርጋሉ? | - | - | 45 | 69.3% | 20 | 30.7% |

ሰንጠረዥ 4.7 የተማሪዎች የጽሁፈ መጠይቅ የመረጃ ትንተና ምላሽ፡-

**ጥያቄ3.1**. በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተራችሁ ላይ በመጻፍ መልሱን እድትገልጹ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 20(26%) አዎን፣ 15(17%) አይደለም፣ 30(57%) አልፎ አልፎ ይከናወናል በማለት መልሰዋል፡፡

**ጥያቄ 3.2.** በድምጽ የተቀረጹ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን አድምጣችሁ መልእክቱን እንድትገልጹ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 7(11%) አዎ፣ 15(23%) አይደለም፣ 50(66%) አልፎ አልፎ እንደሚተገበር ገልጸዋል፡፡

**ጥያቄ 3.3.** ምንባብን ወይም ንግግርን ካዳመጣችሁ በኂላ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተረዳችሁትን አስተያየት እንድትሰጡ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 20(30%)አዎን፣ 13(20%) አይደለም፣ 32 (50%) አልፎ አልፎ የተገበራል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 3.4.** *ሥነፅሑፋዊ ስራዎችን ወደ ክፍል በማምጣት በማስደመጥ መልእክቱን እንድትገልጹ ያደርጋሉ?* **ለሚለዉ መጠይቅ** 45(70%) **አይደለም፣** 20 (30/%) **አልፎ አልፎ ይተገበራል በማለት መልሰዋል፡፡**

**ከዚህ** *ሰንጠረዥ ትንተና መረዳት የሚቻለዉ አብዛኛዉ መጠይቆች የሚተገበሩት አልፎ አልፎ እንደሆነና ጠቂቶቹ ደግሞ የማይተገበሩበት ሁኔታ እንዳለ ያሳያል፡፡*

**ሰንጠረዥ 4. 8፡ የክፍለ ጊዜዉ የድህረ ማዳመጥ ጊዜ አተገባበር በመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና፡፡**

| ተ.ቁ. | የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች | አ ማ ራ ጮ ች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎን | | አይደለም | | አልፎ አልፎ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3 | **ድህረ ማዳመጥ** | | | | | | |
| 3.1. | ተጠኚ ተማሪዎች በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተራቸዉ ላይ በመፃፍ መልሱን እንዲገልጹ ያደርጋሉ? | 1 | 20% | 1 | 20% | 3 | 60% |
| 3.2. | ባደመጡት ርዕሰ ጉዳዩ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያደርጋሉ? | 2 | 40% | - | - | 3 | 60% |
| 3.3. | ባደመጡት ርዕሰ ጉዳይ ዉስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት እንዲለዩና እንዲፅፉ ያደርጋሉ? | 2 | 40% | 1 | 20% | 2 | 40% |

**ሰንጠረዥ 4.8፡-**የድህረ ማዳመጥ ጊዜ አተገባበር ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽና ትንተና ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

**ጥያቄ 3.1.** የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን ወይም ልቦለዶችን በማስደመጥ የርዕሰ ጉዳዩን ጭምቅ ሀሳብ ወይም መልእክት እንዲናገሩ ያደርጋሉ? **ለሚለዉ መጠይቅ** 1(20%) ተጠኚ አዎን፣ 1(20%) ተጠኚ አይደለም፣ 3 (60%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 3.2፡-** ባዳመጡት ርዕሰ ጉዳይ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 2(40%) ተጠኚዎች አዎን፣ 3(60%)ተጠኚዎች ደግሞአለፎ አልፎ እንደሚተገብሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ጥያቄ 3.3.**በሚደመጠዉ ርዕሰ ጉዳይ ዉስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ለይተዉ እንዲፅፉ ያደርጋሉ? ለሚለዉ መጠይቅ 1(20%) ተጠኚ አዎን፣ 1(20%)ተጠኚ አይደለም፣ 3(60%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እተገብራለሁ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት የድህረ ማዳመጥ ክፍለጊዜ የተጠኚ ተማሪዎች የፅሑፍ መጠይቅ ጥያቄ 3.1.እና ሰንጠረዥ ስምንት የተጠኚ መምህራን ቃለ መጠይቅ ጥያቄ 3.1. በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተር ላይ ጽፈዉ መልሱን የመግለጽ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ የተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ፡- 20 (26%) አዎን ፣15 (17%)አይደለም፣ 30 (46%) አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩ መላሽ የሰጡ ሲሆን፤ የተጠኚ መምህራን ቃለ መጠይቅ የተሰጠ ምላሽ ፡-1 (20%) አዎን፣1 (20%) አይደለም፣ 3 (60%) አልፎ አልፎ እንደሚተገበር ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ምክንያት አተገባበሩ ላይ ድክመት አንደሚታይ ያስረዳል፡፡ የድክመቱን ምክንያት ተጠኚ መምህራን ሲገልጹ ተማሪዎቹ የመልመጃ ጥያቄዎቸን መልስ ለመግለጽ ፍላጎት ማጣት፣ ለቋንቋዉ አሉታዊ አመለካከት ማሳየት፣ ተጠኚ መምህራንም የክፍለ ጊዜዉን ይዘት ማጠቃለል ላይ ትኩረት ማድረግን እንጂ ለዚህ ትግበራ ብዙም ጊዜ እንደማይሰጡ ምላሻቸዉን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበዉ ትንተና መገንዘብ የሚቻለዉ አብዛኛዎቹ መጠይቆቹ አልፎ አልፎ እንደሚተገበርና አተገባበሩ ድክመት እንዳለበት ከትንተናዉ መረዳት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

በምዕራፍ አንድ ዉስጥ እንደተጠቀመዉ የዚህ ጥናት ዋና አላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ግምገማ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን የጥናቱም ወሰን በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ የተጠና ጥናት ነዉ፡፡ ይህ ጥናት በአተገባበሩ ሂደት የታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት ደካማ ጎኖቹ የሚሻሻሉበትንና የመፍትሄ አቅጣጫ በመጠቆም የቀረበ ነዉ፡፡

በተጨማሪም በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ በጥናቱ ሂደት ስላጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳሮቶችን በመጥቀስና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመጠቆም ቀርቧል፡፡

### 5.1.ማጠቃለያ

በቋንቋ ትምህርት ሂደት አራቱ የቋንቋ ክህሎትን መማር መሠረታዊ የቋንቋ አዉቀት ማግኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረትም ከነዚህ ከአራቱ ክሂሎች ዉስጥ አንዱ የሆነዉን የማዳመጥ ክህሎት የክፍል ዉስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መገምገም ሲሆን ይሄዉም መምህራን ክህሎቱን እንዲያስተምሩ ተማሪዎችም አዳምጠዉ እንዲረዱት ይዘቶቹን ሲተገብሩት የተወሰኑት አተገባበር ክንዉን ጥሩ ቢሆንም አብዛኛዎቹን የክሂሉን ይዘቶች የሚተገብሩት አልፎ አልፎ እንደሆና አንዳንዱን ደግሞ እንደማይተገብሩት በጥናቱ ዉስጥ ተረጋግጧል፡፡

የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር ከሚቀርቡት ይዘቶች ዉስጥ አሳታፊ የሆኑ ዘቶች ቢቀርቡም ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታቸዉ ጋር የማይጣጣምና ተማሪዎቹም እንደማይሳተፉ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡

የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የክፍል ዉስጥ ትግበራ ያለዉ አስተዋጥኦ ጥሩ ቢሆንም የቤት ሥራ፣ የቡድን ዉይይትና የማዳመጥ ክህሎትን የመተግበር ሁኔታ አልፎ አልፎ እንደሆነ ከጥናቱ ዉጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

መምህራን የማዳመጥ ክህሎትን ለመተግበር የሚያግዙ መሳርያዎችን የተቀረጹ ድምጾችን፣ ስዕል፣ ሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎችንና አጫጭር ታሪኮችን ወደ ክፍል ዉስጥ በማምጣትና ማስደመጥን እንደማይተገብሩ በጥናቱ የፅሑፍ መጠይቅ የተማሪዎች ምላሽ የተገኘ ዉጤት ያሳያል፡፡

የማዳመጥ ክህሎት አተገባበርን ስኬታማ ለማድረግ የመምህራን ሚና ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል፤ ቢሆንም ተጠኚ መምህራን በዚህ ጥናት ላይ የሚጠበቀዉን ሚና በአግባቡመ እንዳልተወጡ በጥናቱ ዉስጥ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተጠኚ መምህራን በክፍል ዉስጥ የማዳመጥ ክህሎትን በሚፈለገዉ መጠን ትኩረት ሰጥተዉ የሚተገብሩት ሳይሆን አልፎ አልፎ እንደማይተገብሩትና ድክመት እንደሚታይበት የጥናቱ ዉጤት ያሳያል፡፡

ሌላዉ በዚህ ጥናት ዉስጥ የታዩ ችግሮች ወይም ተግዳሮቶች፡-መምህራን የተማሪዎችን ወይም የተጠኚዎችን የችሎታ ሁኔታ አለመፈተሽ፣ ከመማሪያ መፅሐፍ ዉጪ ተስማሚ የሆኑ ይዘቶችንና ክንዉኖችን በማዘጋጀት በትግበራዉ ወቅት አለመጠቀማቸዉ፡፡

- የተማሪ መማሪያ መፅሐፉንና የመምህሩን መምሪያ መፅሐፍን እንደ ብቸኛ ማስተማሪያ አማራጭ መጠቀማቸዉ፣
- ተጠኚ ተማሪዎቹ ለቋንቋዉ ትምህርት ያላቸዉ አሉታዊ አመለካከት፣
- የቋንቋዉን ትምህርት ለመማር ፍላጎት ማጣት
- በቋንቋዉ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ዉጤት ዝቅተኛ በመሆኑ የቋንቋዉን ትምህርት የመጥላት፣መምህሩንም አብሮ የመጥላት ስሜት ማሳየት፣
- የተለያዩ ምክንያት በመፍጠር ከመማሪያ ክፍል ጥለዉ መዉጣት፣ የቡድን ዉይይት ሲሰጣቸዉ ከርእስ ዉጪ ወደ ግል ሃሳባቸዉ በመሳብና፣
- ለክህሎቱ ተኩረት አለመስጠት በጥናቱ ሂደት የታዩ ተግዳሮቶች እንደሆነ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳብ

የማዳመጥ ክህሎትን ለማስተማር ተግዳሮት የሚሆኑና በመማር ማስተማሩ ሂደት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምን እንደሆኑ የጥናቱ ዉጤት አሳይታል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በክህሎቱ አተገባበር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነጥቦች የመፍትሔ ሃሳብ ከዚህ በታች ይቀርባል፡፡

1. መምህራን የማዳመጥ ክህሎቱን ለማስተማር ለማዳበር የሚያግዙ ይዘቶችን ከመማሪያ መፅሐፍ ዉጪ በተጨማሪ አጋዥ ይዘቶችን አሻሽሎ በማቅረብ በክፍል ዉስጥ ቢተገብሩ፤
2. መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት በመዳሰስ ከተማሪዎች ችሎታና ፍላጎት ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ ተግባራትን በማዘጋጀት ቢያቀርቡ፤
3. የቋንቋ ትምህርት በክፍል ዉስጥ ብቻ የሚተገበር ስላልሆነ ተማሪዎችን ወይም ተጠኚዎችን ከክፍል ወጪ የተለያዩ ጭውውቶችን፣ ቀልዶችን፣ ተረቶችን፣ … በማስደመጥ የማዳመጥ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ቢያደርጉ፤
4. የማዳመጥ ክህሎት ትምህርትን አዝናኝ ለማድረግና የተማሪዎችን ስሜት መግዛት የሚችሉ የተለያዩ ሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎችን ወደ ክፍል በማምጣትና በማስደመጥ እንዲለማመዱ ቢደረግ፤
5. የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት ዋና ዓላማ የተማሪዎችን አዳምጦ የመረዳት ብቃታቸዉን ማዳበር ስለሆነ ክህሎቱን በሚገባ እንዲለማመዱ ቢደረግ፣
6. መምህራን በመምህሩ መምሪያና በተማሪዉ መማሪያ መፅሐፍ ላይ ጥገኛ ከመሆን የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎችንና አጋዥ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣
7. ተማሪዎች በቋንቋዉ ላይ ያላቸዉ ቋንቋ እውቀት ውስንነት ይቀየር ዘንድ የቋንቋ መምህራን ድርሻ ወሳኝ ነዉና መምህራን በተማሪዎች አእምሮ ላይ የማስተካከል ሥራ ቢሠራ መልካም መፍትሄ ይሆናል፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ማረው ዓለሙ። (1998)። የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ። አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

በድሉ ዋቅጂራ። (1996)። በስነፅሁፍ ቋንቋ ማስተማር። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ነገሰ ገ/ፃዲቅ። (1994)። "9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች፣ መልመጃዎች የክፍል ውስጥ ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ ዘዴ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት።(ያልታተመ)።.

አልማዝ አለማየሁ (2006) በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ፤ በሶስት የአዲስ አበባ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ለተግባራዊ ስነልሳን አማርኛ ለማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

እቴነሽ ተገኝ። (1986)። "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መርሃ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በድህረ ምረቃ ትምህረት መርሃ ግብር። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል። አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ለ2ኛ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት። (ያልታተመ)።

ጥላሁን ከበደ ፦(2003)የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ፤በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ፣በቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አማርኛን የማስተማር ዘዴ (TeAm) ለኤም .ኤድግሪማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

Anderson, A and Lynch. J (1983). Listening. Oxford: Oxford Universi Press

Andersoon; A; & Tory .L, 1988 ;Listening Oxford. Oxford University. Press.

Back.J, 2001 Assessing Listning Cambridge University Press.Cambridje.

Blackwell,A& Naber T.2006 AcadamicListning and Speaking New york Oxford University Press..

Dunn V. and D. Gruber. (1987). Listening Intermediate. Oxford: Oxford University Pres.

Fild. J. 2008. Listning in the Language classroom. Cambridge. UK: Cambridge University Press,

Harmer; Jermy . 1998. How to teach English .Longman; Addition Wesley;First Published.

Http/ inworld.com/ Jhonathan Mark (2018) jornal issue 42/ the five way to teach listening-to-yl-effectively.

Http// eflmagazine.com/ Han Austin (2016) the three-stages of listening activity.

Http/blog.listenwise.com/ Chrsty Swizer (2017).guidelines of teaching listening.

Jonatan marks, (02,2016) /methodology-new-ways to teach listening and practical suggestion of new ways to teach listening

Kral (1996) Teacher Development Making the Right Moves. Washington D.C English LanguagePrograDivision.

Munb ;John 1978 .Communicative Syllabus Design Cambridge; Cambridge University Press.

Richards; J;Listening Cpomprehension Aaa

Rixon. A (1986). Developing Listening Skill. London: Macmillan Publishers Ltd.

Rost; Michael. 1990 Listing in Language Teaching London; Longman Group UK Limited.

Underwood M.(1989). Teaching Listening. London: Longman Group Ltd.

Ur,penny. (1984).*Teching lissing comperation*. Cambridge university press.

Widdowson.H.G (1978). Teaching Language asCommunication.New York: Oxford University Press

# አባሪዎች

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን (2.6) የማዳመጥ ይዘት ምርጫ ስር ምሁራን የተሰጡ ብያኔዎችን በመሰንዘር በይዘቱ ምርጫ ዙሪያ የሚጠበቁ ሀሳቦችን ገልጸዋል፡፡ይሄዉም የማዳመጥ ክሂል ትምህርት በትምህርት ቤት ዉስጥ የማስተማር ዋነኛዉ አላማ ተማሪዉ የሚሰማዉን/የሚያዳምጠዉን ነገር የመረዳት፣የመተርጎም፣የመገምገም የራሱን ምላሽ መስጠት የሚያስችለዉን ክሂሎት ለማስጨበጥ፣በማዳመጥ ችሎታ እንዲተማመንና ህብረተሰቡ ዉስጥ ማዳመጥን ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙ ለማስቻል እንደሆነ (ሽር፣1984፣1-3)ገልጸዋል

ሌላዉ በክለሳ ድርሳን 2.8. የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ መሳሪያዎች በሚል ርእስ ስር ገጽ 23 ላይ(አንደርዉድ 1989) እንደ ገለጹት የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ከሚረዱ ነገሮች መካከል የተቀረጹ ካሴቶች፣ቀጥተኛ የትምህርት ገለጸዎች፣የስነ ጽሁፍ ስራዎች፣ቃለ ምልልሶችና የስልክ ላይ ንግግሮችን እንዲያዳምጡና ካዳመጡት ነገር ተነስተዉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናዉኑ በማድረግ ክሂሉን ማስተማር እንደሚቻልና የማዳመጥ ክሂሉንም ለማዳበር ፋይዳዉ የላቀ መሆኑን ምሁሩ ይገልጻሉ፡፡

በዚህ መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት መጠይቆች በተቻለ መጠን ከላይ የተጠቀሱትን የምሁራንን ብይን ድጋፍ በማድረግ መጠይቆቹ ቀርበዋል፡፡በተጨማሪ አዲሱን የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መጽሀፍእና የቀደምት ስራዎችን አልማዝ(2006 ) ፣ እቴነሽ(1986) እና ጥላሁን (2003) ስራዎችን ደጋፊ ሀሳብ በመጠቀም መጠይቆቹ ተዘጋጅቷል፡፡

## የምልከታ ቅጽ

አባሪ ‹‹ ሀ››

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የክፍል ዉስጥ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባበርን ለመገምገም የተዘጋጀ የምልከታ ቅጽ፡፡

በ‹8ኛ› ክፍል ተመሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ 1ኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበርን ለመገምገም የሚያስችል መረጃን ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ይህንን መረጃ ለመሰብሰብ የተማሪዎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ ጥያቄዉን ለመሙላት ቀና ትብብር እንድታደርጉልኝ በትህትና እጠይቃለሁኝ፡፡

ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር የላቀ ምስጋናዬን ከወዲሁ አቀርባለሁኝ፡፡

መጠይቁን ሲሞሉ፡-

ስም መጻፍ አያስፈልግም

1. ክፍት ቦታዎችን በአጭር አባባል ይመልሱ
2. በሰንጠረዡ ለቀረቡት ጥያቄዎች ‹‹አዎ›› ‹‹አይደለም›› እና ‹‹አልፎ አልፎ››
3. በሚለዉ ስር የ ‹‹X›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

1.መጠይቁ የሚደረግበት ትምህርት ቤት --------------------------------------------------------

2.መጠይቁ የሚደረግበት ክፍል (ምድብ) --------------------------------------------------------

3.መጠይቁየሚደረግበት ቀን-----------------------------------------------------------------

4.መጠይቁ የሚደረግበት ሰአት----------------------------------------------------------------

5.መጠይቁ በሚደረግበት ወቅት የነበረዉ የእለቱ ትምህርት ርእስ------------------------------------

**ማሳሰቢያ፡-** አዎ፣ አይደለም እና አልፎ አልፎ በሚለዉ ስር የ <<X>> ምልክት በማድርግ ይመለሳል፡፡

| ተ ቁ | የጽሁፍ መጠይቆች | አዎ | አይደለም | አልፎ አልፎ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **የቅድመ ማዳመጥ ክንዉን ጊዜ** | | | |
| 1.1 | በቅድመ ማዳመጥ ክሂል ክንዉን ጊዜ መምህራችዉ ርእሱን በሰሌደ ላይ በመጻፍ አስተዋዉቋል? | | | |
| 1.2. | በአዲሱ ፍኖተ ካርታመማሪያ መጽሃፍ ዉስጥ የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ትምህርት ጥያቄዎች ግልጽ ናቸዉ? | | | |
| .1.3. | መምህሩ ርእሱን ካስተዋወቀ በኋላ ስለ ርእሱ ምን ፍሬ ነገር ሊነሱ እንደሚችሉ እንድት ገምቱ ያደርጋሉ? | | | |
| 1.4. | የመማሪያ ክፍል ለክሂሉ ትምህርት ክንዉን ምቹ ነዉ ? | | | |
| | **2.የማዳመጥ ግዜ ክንዉን** | | | |
| 2.1. | መምህራችሁእያንዳንዱን አንቀጽ በእርጋታ ያነቡላችኋል? | | | |
| 2.2. | መምህራችሁ ንግግር ወይም ምንባብ በሚያነቡላችዉ ጊዜ ማራኪነት አለዉ? | | | |
| 2.3. | የተለያዩ ታሪኮችን ወደ ክፍል በማምጣት እንድታዳምጡ ያነቡለችኋል? | | | |
| 2.4. | በማዳመጥ ጊዜ የንግግሩን ወይም የምንባቡን መልእክት እንድትረዱ በቂ ጊዜ ሰጥተዉ ጽሁፉን በድጋሜ ያነቡለችኋል/ | | | |
| | **3. የድህረ ማዳመጥ ክንዉን** | | | |
| 3.1. | በድህረ ማዳመጥ ጊዜ የመልመጃ ጥያቄዎችን በደብተራችሁ ላ በመጻፍ መልሱንነእንድትገልጹ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.2. | በድምጽ የተቀረጹ የማስተማርያ መሳሪያን ካዳመጣችሁ በኋላ መልእክቱን እንድትገልጹ ያደርጋሉ? | | | |
| .3.3. | ምንባብ ወይም ንግግርን ካዳመጣችሁ በኋላ ስለ ርእሰ ጉዳ የተረዳችሁትን አስተያየት እንድትሰጡ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.4. | ስነ ጽሁፋዊ ስራዎችን ወደ ክፍል በማምጣትና ካዳመጣችሁት በኋላ መልእክቱነ እንድትገልጹ የደርጋለ? | | | |

አባሪ ‹ለ›

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርተ

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በስምንተኛ ‹8ኛ› ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የቃለ መጠይቅ / ቅጽ,

የ8ኛ ክፍል የማዳመጥ ክሂል ትምህርት አተገባባርን ለመገምገም ወይም ለመፈተሽ የተዘጋጀ የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ ቅጽ

ይህ መጠይቅ በአርሲ ዞን ዶደታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ 1ኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበርን ለመገምገም የሚያስችል መረጃን ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ይህንን መረጃ ለመሰብሰብ የተማሪዎች ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ መጠይቁን ለመሙላት ቀና ትብብር እንድታደርጉልኝ በትህትና እጠይቃለሁኝ፡፡

ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ከፍ ያለ ምስጋናዬን ከወዲሁ አቀርባለሁኝ፡፡

መጠይቁን ሲሞሉ፡-

ሥም መጻፍ አያስፈልግም

1/ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት ትምህርት ቤት---------------------------------------

2/ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት ክፍል (ምድብ ) ---------------------------------------

3/ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት ቀን---------------------------------------------------

4/ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት ሰአት---------------------------------------------------

5/ቃለ መ ጠይቁ በሚደረግበት ወቅት የነበረዉ የእለቱ ትምህርቱ ርእስ-------------------------

-ክፍት ቦታዎችን በአጭ ር አባባል ይመልሱ

-በሰንጠረዥ ዉስጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች ‹አዎን›‹ አይደለም› ‹አልፎ አልፎ› በሚለዉ ስር የ<X>ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ቃለ መጠይቅ | አዎን | አይደለም | አልፎ አልፎ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቅድመ ማዳመጥ ክንውን | | | |
| 1.1. | መምህሩ በክፈለ ጊዜዉ ክንዉን ስለ ርእሰ ጉዳዩ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ? | | | |
| 1.2. | ለቅድመ ማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያነት የቀረቡ ጥያቄዎች ወቅታዊነትና አዲስነት አለዉ? | | | |
| 1.3. | መምህራችሁ ርእሱን የሚገልጹ ስእሎችና ፎቶ ግራፈፎችን በማሳየት መልእክታቸዉን እንድትገልጹ ያደርጋሉ? | | | |

| ተ.ቁ. | 2. የማዳመጥ ጊዜ ክንዉን | አዎን | አይደለም | አልፎ አልፎ |
|---|---|---|---|---|
| 2.1. | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መጽኃፍ ዉስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ይዘት አቀራረብ ብቃት አለዉ? | | | |
| 2.2. | በማዳመጥ ጊዜ ንግግር ወይም ምንባብ ሲነበብላችሁ በመሀል ቆም በማለት ቀጣዩን ሀሳብ እንድትገምቱ ጊዜ ይሰጣሉ ? | | | |
| 2.3. | መምህሩ የምታዳምጡትን ምንባብ ወይም ንግግር ካከባቢያቸሁ ባህልና ከራሳቸዉ ህይወት ልምድ ጋር እንድታገናዝቡ ያደርጋሉ? | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2.4. | መምህሩ በማዳመጥ ጊዜ ከምንባብ/ንግግር ዉስጥ አዳዲስ ቃላትን ለይታችሁ እንድትናገሩ ያደርጋሉ? | | | |
| 2.5. | መምህሩ በማዳመጥ ጊዜ ክንዉን ቁልፍ ቃላትንና ሀረጋትን በደብተራችሁ ላይ እንድትጽፉ ያደርጋሉ? | | | |
| 2.6. | የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት በማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ቀላል ቋንቋ ይጠቀማሉ? | | | |
| | **3 . የድህረ ማዳመጥ ክንዉን** | | | |
| 3.1. | መምህራችሁ ምንባቡን ወይም ንግግሩን ከዳመጣችሁ በኋላ በርእሱ መሰረት የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በቃላችሁ እንድትመልሱ ያበረታታሉ? | | | |
| 3.2. | ባዳመጣችሁት ርእሰ ጉዳይ ላይ በቡድን እንድትከራከሩና እንዲሰሩ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.3. | ካዳመጣችሁት ርእሰ ጉዳይ የተረዳችሁትን ጭምቅ ሀሳብ በጽሁፍ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.4. | ካዳመጣችሁት ንግግር ወይም ምንባብ ለወጡት ቃላት ተመሳሳይ፣ ተቃራኒ ወይም አዉዳዊ ፍች እንድትሰጡ ያደርጋሉ? | | | |

አባሪ ‹ሐ>

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎችጥናጥ፣የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛቋንቋ ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የቃለ መጠይቅ ቅጽ ይህ ቃለ መጠይቅ በአርሲ ዞን ፣ ዶዶታ ወረዳ፣አርጊቲ ደነባ 1ኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤት ዉስጥ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል የክፍል ዉስጥ አተገባበርን ለመፈተሽ የሚያስችል መረጃን ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ ይህንን መረጃ ለመ ሰብሰብ የመምህራን ተሳትፎ ስፈላጊ በመሆኑ መጠይቁን ለመሙላት ቀና ትብብር ስላደረጋችሁልኝ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁኝ፡፡

መጠይቁን ሲሞሉ፡-

ስም መጻፍ አያስፈልግም

ክፍት ቦታዎችን በአጭር አባባል ይመልሱ

በሰንጠረዡ ዉስጥ ለቀረቡት መጠይቆች ‹‹አዎን›› ‹‹አይደለም›› እና ‹‹አልፎ አልፎ››በሚል ስር የ‹‹ ›› ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡

-መጠይቁ የሚደረግበት ትምህርት ቤት------------------------------------------

-መጠይቁ የሚደረግበት ክፍል (ምድብ)----------------------------------------------

-መጠይቁ የሚደረግበት ቀን -----------------------------------------------------

-መጠይቁ የሚደረግበት ሰአት---------------------------------------------------

-መጠይቁ በሚደረግበት ሰአት የነበረዉ የትምህርት ርእስ--------------------------

‹‹አዎ›› ‹‹አይደለም›› እና ‹‹አልፎ አልፎ››በሚለዉ ስር የ(X) ምልክት አስቀምጡ።

| ተ.ቁ | የምልከታ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች | አዎ | አይደለም | አለፎ አልፎ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **የቅድመ ማዳመጥ ክንዉን** | | | |
| 1.1. | የማዳመጥ ክሂል ትምህር በክፍል ዉስጥ ለተማሪዎች መቅረቡ ተገቢ ወይም አስፈላጊ ነዉ ብለዉ ያምናሉ ? | | | |
| 1.2. | በቅድመ ማዳመጥ ክፍለ ጊዜ ርእሱን በሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለተማሪዎች ያስተዋዉቃሉ? | | | |
| 1.3. | በቅድመ ማዳመጥ ክፍለ ጊዜ አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳሉ? | | | |
| 1.4. | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መጽሀፍ ዉስጥ የቀረቡ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ብቁና ግልጽ ናቸዉ ? | | | |
| | 2. **የማዳመጥ ጊዜ ክንዉን** | | | |
| 2.1. | በአዲሱ ፍኖተ ካርታ መማሪያ መጽኅፍ ዉስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ጥያቄዎች ቁልፍ ቃላትንለማስተማር ብቃት አላቸዉ ? | | | |
| 2.2. | በማዳመጥ ጊዜ ምንባብ ወይም ንግግርን እያስደመጡ በመሃል ቆም እያሉ ቀጣዩን ሃሳብ እንዲገምቱ ያደርጋሉ? | | | |
| 2.3. | ለክሂሉ ማስተማሪያነት የተቀረጹ ድምጾችን ፣ ስእል፣ ካርታና በሰንጠረዥ መልክ የተዘጋጁ የትምህርት መርጃዎችን በክፍል ዉስጥ ይጠቀማሉ ? | | | |
| 2,4. | በማዳመጥ ጊዜ የሚደመጠዉነወ ርእሰ ጉዳይ ከራሳቸዉ ልምድና ከአካባቢያቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያመሳክሩ ያደርጋሉ / | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3. **የድህረ ማዳመጥ ጊዜ ክንዉን** | | | |
| 3.1. | የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን ወይም ልቦለዶችን ካስደመጡ በኂላ ስላዳመጡት ታሪክ መልእክት በአጭሩ እንዲገልጹ ያደርጋሉ ? | | | |
| 3.2. | ስለዳመጡት ርእሰ ጉዳይ ላይ በግል ፣ በጥንድ፣ በቡድን በማመቻቸት እንዲወያዩ ያደርጋሉ? | | | |
| 3.3. | ባዳመጡት ንግግር ወይም ምንባብ ዉስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ለይተዉ እንዲጽፉና ፍች እንዲሰጡ ያደርጋሉ? | | | |
| .. | ? | | | |

# ማረጋገጫ

"አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች የክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ፤በአርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት" ርዕስ ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት በማንኛውም አካል ያልተሰራና ወጥ የራሴ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም ---------------------------------------------

ፊርማ --------------------------------------------

አድራሻ -------------------------------------------

ቀን ----------------------------------------------